# የሕግየበላይነት

## ለፖለቲከኞች የተዘጋጀ መመርያ

HiiL innovating justice

RAOUL WALLENBERG INSTITUTE
OF HUMAN RIGHTS AND HUMANITARIAN LAW

**የቅጂ መብት ©**

**የራውል ዋለንበርግ የሰብዓዊ መብት እና የጦርነት ሰብዓዊነት ሕግ ኢኒስቲትዩት እና**

**የሄይግ የህግ ዓለምአቀፋዊነት ኢኒስቲትዩት 2012**

**ISBN: 978-91-86910-71-6**

ይህን ሕትመት ለንግድም ሆነ ለሌላ ዓላማ ማዋስ፣ መሸጥ፣ ማከራየት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ያአሳታሚው ፈቃድ በማናቸውም ከታተመበት በተለየ ጥራዝ፣ ልባስ ወይም ሁኔታ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ይህ ሁኔታ በቀጣይ አሳታሚ ላይም ይጸናል፡፡

ይህንን መመሪያ አሳታሚው እስከፈቀደ፣ መቅድሙ እስከተካተተና ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ መተርጎም ይቻላል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የሚተረጉሙ በነጻ ሥራውን እንዲያከናውኑ ይበረታታሉ፡፡ አሳታሚዎቹ ትርጉሞቹን በድረገጻቸው ላይ ለመስቀል እንዲችሉ ለሚሰጣቸው ቅጂ ሁሉ በቅድሚያ ምሥጋና ያቀርባሉ፡፡

አሳታሚ

The Raoul Wallenberg Institute of Human Rights and Humanitarian Law

Stora Grabrodersgataan 17B

P.O. Box. 1155

SE-221 05 Lund

Sweden

Phone: +46 46 222 12 00

Fax.  +462221222

E-mail: rolf.ring@rwi.lu.se

www.rwi.lu.se

The Hague Institute for the Internationalisation of Law (HiiL)

Anna van Sakseniaan 51

P.O.Box. 93033

2509 AA The Hague

The Netherlands

Phone: +31 70 349 4405

Fax: +31 70 349 4400

E-mail: info@hiil.orgwww.hiil.org

ልባስ፤ ፐብሊማርኬት ቢ.ቪ፣ ኔዘርላንድስ

# የሕግ የበላይነት

## ለፖለቲከኞች የተዘጋጀ መመርያ

### ማውጫ


መቅድም ..... 5

1.መግቢያ ..... 6

2.የሕግ የበላይነት በሀገር ደረጃ ..... 7

2.1 የሕግ የበላይነት ትርጉም በሀገር ደረጃ ..... 7

2.2 በብሔራዊ ደረጃ ለሕግ የባለይነት የሚስፈልጉ ሁኔታዎች ..... 11

2.2.1 ሕገ-መንግስታዊነት ..... 11

2.2.2 ለህዝብ ይፋ ማድረግ (ማሣተም) ፣ግልፅነት፣ ወደ ኃላ ተመልሶ አለመስራት እና መረጋጋት (አለመዋዠቅ) ..... 11

2.2.3. የፓርላማዎች ልዩ ኃላፊነት ..... 13

2.2.4. የመወሰን ስልጣን ..... 14

2.2.5. የስልጣን ክፍፍል ..... 14

2.2.6. ፍርድ ቤቶች ..... 15

2.2.7. አማራጭ ሙግት መፍቻዎች ..... 18

2.2.8. ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት ..... 19

2.2.9. በቂ የሆነ አተገባበር ..... 19

2.2.10 ጥንቃቄዎች ..... 19

2.3. በሀገር ደረጃ የሕግ የበላይነት መሥፈን ለምን የግድ ይላል ..... 21

2.3.1 የሥልጣን ገደብ ..... 21

2.3.2 የህግ እርግጠኝነት (ግልፅነት) እና ነፃነት ..... 22

2.3.3 በእኩልነት መታየት ..... 23

3. በዓለምአቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነት አሰፋፈን ..... 23

3.1. የህግ የበላይነት ትርጉም በአለምአቀፍ ግንኙነቶች ውስጥ ..... 23

3.2. በዓለምአቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች (መስፈርቶች) ..... 25

3.2.1. ዓለምአቀፍ ሕግ ግልፅ፣ ይፋ፣ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል (ተደራሽ) እና አመላካች መሆን አለበት ................................ 25

3.2.2 ገለልተኛና ነጻ ፍርድ ቤት ........................................................................................................... 26

3.2.3 በቂ የሆነ የፍርድ (የሕግ) አፈጻጸም ............................................................................................ 28

3.3. የሕግ የበላይት ለምን በዓለምአቀፍ ደረጃ የግድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ....................................................... 29

4. በብሔራዊና በዓለምአቀፍ ደረጃዎች ያሉ የሕግ የበላይነት ስርዓቶች መካከል ያለው ትሰሰር ............................................ 30

4.1. በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ....................................................................................................... 30

4.2 በአገር ውስጥ ያለው የሕግ የበላይነት ለምን በዓለምአቀፍ ሕግ ላይ ጥገኛ ይሆናል? ....................................................... 32

4.3 በዓለምአቀፍ ደረጃ ያለው የሕግ የበላይነት በብሔራዊ ሕግ ላይ ለምን ጥገኛ እንደሚሆን............................................... 35

5. ተጨማሪ ምንባብ ምንጮች ......................................................................................................................... 38

# መቅድም

የዚህ መመሪያ አላማ ፖለቲከኞችን ከሕግ የበላይነት ዋና ዋና ገጽታዎች ጋር ማስተዋወቅ ነው፡፡

ለዚህ መመሪያ መነሻ የሆነው በቀድሞ ርዕሳነ ብሔራትና መንግስታት የጋራ ምክር ቤት ውስጥ የተደረጉ ውይይቶች ናቸው፡፡ ይህንን ጽሑፍ የማዘጋጀት ሥራ ያስጀመሩት እና ተከታትለው ያሰሩት በስዊድን ሃገር በሉንድ ዩኒቨርስቲ የሚገኘው የራውል ዋለንበርግ ኢንስቲትዩት ኦፍ ሂውማን ራይትስ ኤንድ ሂውማኒታሪያን ሎው የተባለው እና በኔዘርላንድ ሀገር የሚገኘው ዘ ሄይግ ኢንስቲትዩት ፎር ዘ ኢንተርናሽላዜሽን ኦፍ ሎው የተሰኘው ናቸው፡፡

የዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ረቂቅ የተዘጋጀው በዘሄይግ ኢንስቲትዩት ፎር ዘኢንተርናላይዜሽን ኦፍ ሎው ውስጥ የሕግ የበላይነት ፕሮግራም ኃላፊ በዶ/ር ሮናልድ ጃንሴ ሲሆን በኔዘርላንድ የሰብዓዊነትና የማህረሰብ ሳይንስ ከፍተኛ ጥናት ኢንስቲትዩት ውስጥ በሄንሪ ጂ ሽርመርስ ስም በሚጠራው ፕሮግራም ስር በተመራማሪነት እና በአስተማሪነት በሠሩበት ወቅት ነው፡፡ ከዚያም በሁለቱ አሠሪ (ተቆጣጣጣሪ) ተቋሞች አማካኝነት ተጨማሪ ሥራ ተሰርቶል፡፡ በመቀጠልም በጋራ ምክር ቤቱ አባላትና በፓርላማዎች ህብረት ተወካዩች አማካኝነት ከእንደገና ታይቷል፡፡ ከግለሰብ ባለሙያዎችም ጠቃሚ አስተያየት ተገኝቷል፡፡ በመጨረሻም በዶ/ር ሀንስ ኮረል የራውል ዋለንበርግ ኢንስቲትዩት ባለአደራ ቦርድ ሊቀመንር እና የተባበሩት መንግስታት የቀድሞ የሕግ አማካሪ አማካኝነት በድጋሚ ተመርምሯል፡፡

ሥራ የሚበዛባቸው ፖሊቲከኞች ጽሑፉን ማንበብ እንዲችሉ በተቻለ መጠን ማጠር አለበት የሚለው ጽሑፉን ለማዘጋጀት መሪ መመሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ሆኖም ለሎሎች ውሳኔ ሰጪዎች፣ፖሊሲ አውጪዎች፣ጋዜጠኞችና በርዕሰ ጉዳዩ ግንዛቤ ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ የሚያገለግል መሆን አለበት፡፡ መመሪያው ወደ ሌሎች ቋንቋዎች በቀላሉ ሊተረጎምና ሊታተም የሚችል መሆንም አለበት፡፡ በመመሪያው ውስጥ ስዕሎች እና ሠንጠረዦች ያልተካተቱትም ለዚህ ነው፡፡

መመሪያው ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መቅድም እስከተካተተ እና እስካልተዛባ ድረስ ይህንን ጽሑፍ ኢንስቲትዩቶቹን በማስፈቅድ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም ይቻላል፡፡ የሥራው ዋና ቅጂ በአሰሪዎቹ ኢንስቲቲዩት ድረ ገጽ ላይ የሚገኝ ሲሆን ትርጉሞቹም ይታተማሉ፡፡

ሉንድ እና ሄይግ እ.ኤ.አ. ኦቆጣጠር 2012

ስለ ራውል ዋለንበርግ ኢንስቲትዩት ኦፍ ሂውማን ራይትስ ኤንድ ሂውማኒታሪያን ሎው

**ማሪ ቱማ**

**ዳይሬክተር**

ስለ ሄይግ ኢኒስቲትዩት ፎር ዘ ኢንተርናሽላይዜሽን ኦፍ ሎው

**ሳም ሙለር**

**ዳይሬክተር**

## 1. መግቢያ

የሕግ የበላይነት የዓለም ሁሉ የትልቅነት መለኪያ እና ራዕይ እየሆነ መጥቷል፡፡ ህዝብ፣ መንግስት እና በዓለም ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ይደግፉታል፡፡የሀገር ውስጥ የአስተዳደራዊ እና የሕግ ሥርዓቶች የማዕዘን ራስ ነው ተብሎ በሰፋት ይታመናል፡፡ በዓለም አቀፍ ግንኙነቶችም ውስጥ አስፈላጊነቱ ይበልጥ እውቅና እያገኘ ነው፡፡

በእ.ኤ.አ 2005 የዓለም ስብሰባ ሰነድ ላይ ርዕሳነ ብሔራት እና መንግሥታት የሕግ የበላይነት በብሔራዊም ሆነ በዓለም በሙሉ እንዲከበር ላለው ፍላጎት ዕውቅና ለመስጠት ተስማምተዋል፡፡ ከዓመት በኋላየየተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በብሔራዊም ሆነ በዓለምአቀፍደረጃ ስለሚኖር የሕግየባላይነት ውሣኔ ከማሳለፉም በላይ ከዚያ ወዲህ በዓመታዊ ስብሰባው ይህንን ማድረግ ቀጥሏል፡፡

የጠቅላላ ጉባኤው እ.ኤ.አ በ2010 ላይ እኤአ በ2012 የሚደረገው የ67ኛ ስብሰባ አካል በሆነው የከፍተኛ ደረጃ ስብሰባ ላይ በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስሚኖር የሕግ የበላይነት በተመለከተ የጠቅላላ ጉባዔው የከፍተኛ ደረጃ ስብሰባ እንዲካሄድ ውሣኔ አሳልፏል፡፡

የዚህ መመሪያ ዓላማ ስለሁለቱም ደረጃዎች የሕግ የበላይነት መሠረታዊ ማብራሪያ መስጠት ነው፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የሚኖርየሕግ የበላይነት በተወሰነ ደረጃ በዓለምአቀፍ የሕግ የበላይነት ላይ ጥገኛ መሆኑ እና ይህ አባባል በተቃራኒውም እንደሚሠራም ያስረዳል፡፡ የመመሪያው መነሻ እ.ኤ.አ በጁን 2005 በቀድሞ ርዕሳነ ብሔራትና መንግሥታት የጋራ ምክር ቤት አባላት የተደረገው ውይይት ነው፡፡ እ.ኤ.አ ከጁን 25-27ቀን 2005 በስቶኮልም ስዊድን በተካሄደው 26ኛ የም/ቤቱ አጠቃላይ ስብሰባ መጨረሻ ባወጡት መግለጫ ላይ ከዳሰሷቸው መካከል በተለይ ‹‹ዓለም አቀፍሕግን መመለስ›› የሚለው ይገኝበታል፡፡

ከጋራ ም/ቤቱ ድረገፅ ላይ ለመረዳት እንደሚቻለው ም/ቤቱ ቀደም ሲል በሀገራቸው ከፍተኛውን የመንግሥት ሥልጣን ይዘው የነበሩ ሰዎች ያካበቱትን ልምድ፣ ዕቅድ እና ትውውቅ ለመጠቀም ታስቦ እ.ኤ.አ. በ1983 (1975-1976 ዓ.ም) የተቋቋመ ነፃ ተቋም ነው፡፡የምክር ቤቱ አባላት በጋራ ሆነው የሰውን ልጅ ለሚያጋጥሙት የአስተዳደር (የፓለቲካ)፣ የምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ) እና ማህበራዊ ችግሮች ሁሣብ እና ተግባራዊ መፍትሄ አቅርበዋል፡፡

የም/ቤቱ የእ.ኤ.አ 2008 የአቋም መግለጫ በሚዘጋጅበት ወቅት ፓሊቲከኞች ስለ ሕግ የበላይነት ትርጉም እና ስለዓለምቀፍ ሕግ ያላቸውን መሠረታዊ ግንዘቤ ማሳደግ እንደሚገባ ተሠምሮበታል፡፡

ይህ ሃሳብ በራውል ዋለንርግ ኢንስቲትዩት አፍ ሂውማን ራይትስ ኤንድ ሂውማኒቴሪያን ሎው እና በዘ ሄይግ ኢኒስቲትዩት ፎር ዘ ኢንርናሽናላይዜሽን አፍ ሎው አማካኝነት ዳብሯል፡፡ ይህ በዓለም የፍትሕ ፕሮጀክት አማካኝነት በተዘጋጀው ስብሰባ ላይም ተነስቶ ነበር፡፡ ይህንን መመሪያ የሚያነቡ ሁሉ ሀገራቸው ከግርጌው በተያያዘው የሰብዓዊ መብት ኢንዴክስ ላይ እንዴት እንደተመዘነች ማየት ይችላሉ፡፡

በዚህ ሂደት በ1889 እ.ኤ.አ የተቋቋመው (ዓለም አቀፍ የፓርላማዎች ህብረት) ተሳትፏል፡፡ አ.ፓ.ህ ለአለማቀፍ ፓርላማዊ ውይይት፣ ሰላምና ትብብር በህዝቦች መካከል እንዲኖርና ሕዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት የሚሳተፍበት የዲሞክራሲ ሥርኣት እንዲመሠረት ይሠራል፡፡ ከአፓህ ዓላማ አንዱ ስለሕዝብ ተወካይ ተቋማት አሠራር የተሸለ ግንዛቤ እንዲፈጠር አስተዋጽ ማድረግ እና የሚሠሩበትን መንገድ ማጠናከርና ማዳበር ነው፡፡

ከመግቢያው ላይ ለማየት እንደሚቻለው የእነዚህ ተቋማት ወኪሎች ይህንን መመሪያ ለማዘጋጀት በንቃት ተሳትፈዋል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ በእርግጥ ብዙ ጹሁፎች በቀላሉ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በጉዳዩ ለይ አጠር ያለ ማብራሪያ ማቅረብ ጠቃሚ እንደሆነ ታምኗል፡፡ ይህም ሥራ የሚበዛባቸው ፖለቲከኞች የራሳቸውን ሚና እና ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋጽኦ እያሰቡ በቀላሉ ግንዛቤ እንዲወስዱ ይረዳቸዋል፡፡

ይህንን መመሪያ ያዘጋጁት ተቋማት መመሪያው ከዓለም ላይ የጥቂት ሀገሮችን የሕግ ሥርዓት ብቻ የሚመለከት ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል ይረዳሉ፡፡ ነገር ግን ይዘቱ ለሚመከተው ሁሉ እንደሚጠቅም ተስፋቸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢፓህ ባቀረበው ሰነድ በማጣቀሻት በተገለጽት ጽሑፎች ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጓል፡፡

በሌላ አቅጣጫ መመሪያው በማዕከል ደረጃ በሚገኙ ፖለቲከኞች ለይ ትኩረት አድርጎ ነገርግን በክልል በክ/ሀገር ደረጃ ባሉ ባልደረቦቻቸው ላይ ጥቂት ትኩረት የሰጠ ተደርጎ ሊወሰድ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ በእርግጥም የማይቀር ነው፡፡ ነገርግን በእነዚያ ደረጃ እያገለገሉ ለሚገኙ ፖለቲከኞች መመሪያው ጠቃሚ እንዲሆነ መመሪውን ያዘጋጁት ተቋማት ያምናሉ፡፡

## 2.የሕግ የበላይነት በሀገር ደረጃ

### 2.1 የሕግ የበላይነት ትርጉም በሀገር ደረጃ

#### 2.1.1 የሕግ የበላይነት ምንድን ነው?

በይዘት የሕግ የበላይነት ማለት ዜጎችና እነርሱን የሚያስተዳድራቸው ለሕግ መታዘዝ አለባቸው ማለት ነው፡፡ ይህ ቀላል ትርጉም ጥቂት ማብራሪያ ይፈልጋል፡፡ ለምን አይነት ጉዳዮች ነው የሕግ የበላይነት ተፈፃሚ የሚሆነው? ሕግ ማለት ምን ማለት ነው?

የሕግ የበላይነት ተፈጻሚ የሚሆነው በአንድ በኩል በሀገር ባለሥልጣናት (መንግስትና ሌሎች በተለያዩ ደረጃ ያሉ የአስፈጻሚ አካላት እና ፍ/ቤቶች) እና በሌላ በኩል በዜጎች ፣በነዋሪች እና በሌሎቹ እንደ ማህራትና ድርጅቶች ባሉ የግል ተቋማት መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ሕጎች እንዴት መውጣት እንዳለባቸው ወይም ግብር እንዴት መጣል እና መሰብሰብ እንዳለበት ነው፡፡
የህግ የበላይነት በማህበረሰብ ውስጥ በግል ተዋናዮች መካከል በሚካሄደውም ይፈፀማል:: ንብረት እንደ መግዛትና መሸጥ ላሉ ነገሮች አግባብነት አለው፡፡ የተንቀሳቃሽ ስልክ ይሁን ወይም መኪና መግዛት

መሸጥ ወይም በትራፊክ አደጋ በደረሰ ጉዳት ካሣ፣ በቤተሰብ ግንኙነት እንደ ጋብቻ፤ፍቺ፤ውርስ ወይም መሬትን አርሶ የመጠቀም፤መግዛት ወይም መሸጥ ጉዳዩችም ጋር ይገናኛል፡፡

በአጭሩ የሕግየበላይነት በገዢዎችና በተገዢዎች መካከል ባለው ግንኙነትም ሆነ እንደ ማህበራትና ኩባንያዎች ባሉየሕግ ሰዎች ወይም የተፈጥሮ ሰዎች በመሣሠሉ የግል አካላት መካከል ባለው ግንኙነት ላይ አግባብነት አለው፡፡ ይህ በጣም ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ የሕግ የበላይነት የሚመለከተው የመንግስት ስልጣን አጠቃቀምን ከመገደብ ጋር በተያያዘ ብቻ ነው ብለው የሚከራከሩ ስላሉ ነው፡፡ ነገር ግን አይደለም፡፡

ይህ ከተባለ ከላይ ባሉት ግንኙነቶች ውስጥ ያለው የሕግ የበላይነት ተፈፃሚነት ሰፊ ልዩነት አለው፡፡ ሕግ እስከምን ድረስ በማህረሰብ ጉዳዮች ውስጥ መግባት አለበት የሚለውን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶችአሉ፡፡ ሕዝቦቻቸው ደህንነት ላይ የሚያተኩሩ መንግስታት የመንግስትን በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ የበዛ ቁጥጥር ይደግፋሉ፡፡ በሌላ በኩል ሊበራል (የማያጠብቁ) የሚባሉ መንግስታት ለመንግስት ቁጥጥር መጠነኛ ቦታ ይሰጣሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ባለንበት ዘመን የመንግስት ዓላማ ሕግና ሥርዓትን ማስከበር ብቻ ሊሆን እንደማይችል መታወቅ አለበት፡፡ የሕግ የበላይነት ከሰብዓዊ መብት መጠበቅ ጋር መያያዙ መንግስት የተወሰኑ ማህራዊ ተግባሮችን በተመለከተ ኃላፊነት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ይህ ማለት የሕግ የበላይነት መንግስት የተወሰኑ ማህራዊ ግንኙነቶችን አኮኖሚያዊውን ጨምሮ ሕግ እንዲያወጣ እና እንዲቆጣጠር ይፈልጋል፡፡ የቁጥጥሩ ልክ ከሀገር ሀገር እና በተወሰነ ደረጃ መንግስት በሕዝቡ እንደሚኖረው አመኔታ መጠን እንደሚለያይ ግልፅነው፡፡ በጥቂት አገሮች ብዙ ማህበራዊ ግንኙነቶች ከፍተኛ የህግ ቁጥጥር አለባቸው፤ በሌሎች ማህበረሰቦች ሕግ በጣም ውሱን ወይም ዝቅተኛ ሚና አለው፡፡ ነገር ግን ብዙ ቁጥጥር የሚያደረጉ መንግስታት እንኳን ሳይቀሩ በማህረሰቡ ውስጥ የሚደረገውን ሁሉ በሕግ ቁጥጥር ማድረግ የማይችልና የማያስፈልግ መሆኑን ያምናሉ፡፡ ሌሎች አይነት ደንቦች ብዙ ግዜ አግባብነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሀይማኖታዊ ደንቦችን፣ አብሮ የመኖር ወጎችንና የቢዝነስ/የንግድ/ ደንቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡

በአጭሩየሕግ የበላይነት በዜጎች ውስጥ ወይም በሌሎች የግል አካላት መካከል ለሚደረጉ ግንኙነቶች በሙሉ አግባብነት አለው ለማለት አይቻልም፡፡ ነገርግን የመንግስት ስልጣንን አጠቃቀም በተመለከተ ሁሉጊዜ የሕግ የባለይነት መመዘኛ ነው፡፡ በዚህ ምንም ልዩ ሁኔታ የለም፡፡ በመጀመሪያ የመንግስት ባለስልጣናት ስልጣናቸውን ለመጠቀም በህግ የተሰጠ ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ለምሣሌ አንድ ባለስልጣን ቤት ለመበርበር ከፈለገ አግባብነት ያለው በሕግ የተሰጠ ስልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ ማለትም ሕጉ የትኛው ባለስልጣን የትኛውን ስልጣን በየትኛው ሁኔታ መጠቀም እንዳለበት ይወስናል፡፡ሁለተኛ ስልጣንን ሲጠቀሙ ባስልጣናት ሕግን ማክበር አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በብዙ ሐገሮች ሰው ሲታሰር ባስልጠኑ የእስር ትዕዛዝ ሊኖረውና የሚታሠረውንም ሰው ለምን እንደሚታሠር መንገር አለበት፡፡ ተጠርጣሪውየሚናገረው ነገር ሁሉ በእርሱ ለይ በፍ/ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው ይገባል፡፡

ይህ ‹‹ዳኝነት በተገቢው ማየት›› ተብሎ ሊጠራ የሚችል ሲሆን ዓላማውም ለምሣሌ ሰዎች ያለክስ እንዳይታሠሩ፣ ሲታሠሩም ወይም ሲከሰሱም ጠበቃ እንዲያማክሩ እና በአጠቃለይ መብታቸው እንዲከበር ነው፡፡

ለማጠቃለል የሕግ የበለይነት የመንግስትን የሥልጣን አጠቃቀም በሕግ ሥር የሚያስገባ እናበግለሰቦች መካከልና በግል አካላት ግንኙነቶች ውስጥም የሚገባ ነገር ነው፡፡

## 2.1.2 የሕግ የበላይነትና የፖለቲከኞች ሃላፊነት

የፖለቲካ ሥልጣን በሕግ ሥር መሆኑ ለተራው ሰው ከዚህ በታች በተገለጹት ምክንያቶች በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ መንግሥት ልክ እንደ አምባገነን የፈለገውንና ደስ ያለውን ማድረግ የሚችል ከሆነ መልካም ነገር አይደለም፡፡ ለዜጎች ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች ወንድሞቻቸው ከህግ በታች መሆናቸው በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ምክንያቱም ሕግ ከግለሰቦች የግል ደህንነትና ነፃነት ጀምሮ አስተማማኝ የንግድ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል የተረጋጋ እና ምቹ መኖሪያ ስለሚፈጥር ነው፡፡
ነገር ግን የሕግ የበላይነት ሲባል ብዙ ሕጎችንና ደንቦችን በማውጣት መላውን ወይም አብዛውም የዜጎችን እንቅስቃሴ መቆጣጠር ማለት አይደለም፡፡ በተቃራኒው ዜጎች እንቅስቃሴያቸው ሙሉ በሙሉ በሕግና በደንብ ቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ የማይፈልጉበት በቂ ምክንያት አላቸው፡፡ ሕግ በበዛ ቁጥር ሰው የሚፈልገውን እንዳያደርግ ይገድባል፡፡

በሌላ በኩል ግን ፓለቲከኛው (ፖሊሲ አውጪው) አንዳንድ ጊዜ የተለየ አቋም መውሰድ ይኖርበት ይሆናል፡፡ አንዳድ ጊዜ ከሕግ የበላይነት መርህ አንፃር ሲቃኝ የሕግ አለመኖር እንደ ድክመት፣ጉዳት፣ አደጋ እና ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ባሥልጣኖች ግልጽ ሕግ በሌለበት ሁኔታ ቅጣት ሊወስኑ ወይም ሊጥሉ አይገባም፡፡ እንዲሁም በሕግ የተሰጠ ሥልጣን ሳይኖራቸው እና በግልፅ በተደነገገ ሕግ ሳይመሩ ጥቅሞችን ሊያከፍፍሉም ሆነ ስጦታ ሊሰጡ አይገባም፡፡
የፓለቲካ ሰው ሌሎች ፓሊሲ አውጪዎች እና ባለሥልጣናት እንደፈቀዳቸው ሥልጣናቸውን አለመጠቀማቸውን መከታተል አለበት፡፡ ፓሊቲከኛ የፈለገውን መሥራት አለብኝ የሚል ሳይሆን ሥልጣኑ በሕግ መገደቡ የሚያስደስተው መሆን አለበት፡፡ ፖሊቲከኛ ሥልጣንን በሕግ ብቻ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበት ሥርዓት እንዲመጣ መታገል አለበት፡፡
ፓለቲከኞች በሥርዓቱ ያላቸው ቦታ የትም ይሁን የት እንኳስ እራሳቸው ቀርቶ ሌሎች ሹመኞች በሕግ ባልተሰጣቸው ሥልጣን በመሥራትም ሆነ ወይም በተሰጣቸው ሥልጣን ያላግባብ በመገልገል ሕግን እንዳይጥሱ መከላከል አለባቸው፡፡
ይህ በተለይ በአስፈፃሚው የመንግስት አካል ውስጥ ለሚሠሩ የፖለቲካ ተመራጮች አግባብነት አለው፡፡ ነገር ግን የሕግ የበላይነት ሁሉም ወይም አብዛኛው የዜጎች ባህሪ ለብዙ ሕጎችና ደንቦች እንዲገዛ አይፈልግም፡፡ በታቃራኒው ዜጎች ኑሯቸው ለብዙ ሕግ እና ደንቦች ተገዢ እንዳይሆን የሚቃወሙበት በቂ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ብዙ ሕግ ማለት አነስተኛ ነጻነት ማለት ነው፡፡
በሌላ በኩል ፖለቲከኞች እንደ ፖሊስ አውጪ የተለየ አቋም ሊወስዱ ይችላሉ፡፡
በሕግ አውጪነት የሚሰሩ ፖለቲከኞች ሥልጣን በአጥጋቢ ሁኔታ መገደቡን ዘወትር ልብ ማለት (መቆጣጠር) አለባቸው፡፡ ለባለሥልጣን እንደልብ ለመወሰን የሚያስችል ሠፊ ሥልጣን ተሰጥቶ ካዩ ሕጉን የማስተካከል ኃላፊነት ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለማችን በፀረሽብር ዙሪያ የሚወጡ ድንጋጌዎች ለሰፊ ትርጉም የመጋለጥ አደጋ ያንዣበበባቸው እና መሠረታዊ መብቶች በቀላሉ የሚሸረሸሩባቸው ቦታዎች መሆናቸው ታይቷል፡፡ የፖለቲከኛ ኃላፊነት ሥልጣኑ ምንም ይሁንምን የመንግስት ስልጣን በሕግ ሥር መሆኑንና ሥልጣኑም በሕግ መሰረት በተግበሩን ማረጋገጥ ነው፡፡

### 2.1.3. የሕግ የበላይነትን የሚያቋቁሙ ሦስት ነገሮች ሕጋዊነት፣ ዲሞክራሲ እና ሰብአዊ መብቶች

የሕግ የበላይነትን ትርጉም በተመለከተ መጠየቅ ያለበት አስፈላጊው ጥያቄበትክክል ‹‹ህግ›› የሚለው ቃል ‹‹የሕግ የበላይነት›› በሚለው ሀረግ ውስጥ ያለው ትርጉም ነው፡፡ በመጀመሪያ በ‹‹የሕግ የበላይነት›› ውስጥ ሕግ የሚለው የሚመለከተው የተወሰኑ ሥርዓቶችን ያሟላ ድንጋጌንመሆኑግልጽ ነው፡፡

መሟላት ያለባቸው ሥርዓቶች ስንል ስለ ይዘቱ ሳይሆን ለምሣሌ አንድ ሕግ በመንግስት የወጣ መሆኑን የሚያሳዩ ገጽታዎችን መያዝ፣ ሕግ በሚታተምበት ብሔራዊ (ነጋሪት) ጋዜጣ መውጣት፣ ሕዝብ ሊረዳው በሚችል ሁኔታ መፃፍ መገለጽ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ገጽታ ሕጎች ከሚወጡበት መንገድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሁለት ሰፊ አማራጮች አሉ፡፡ ሕጎች በተመረጡና ለሕዝብ ተጠሪ በሆኑ ሰዎች ሊወጡ ወይም ባልተመረጡ ሰዎች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡ በዲሞክራሲያዊ ወይም ዲሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ሊወጡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የህግ የበላይነት ሙሉ ለሙሉ ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው በዲሞክራሲያዊ የፖሊቲካ ሥርዓት ብቻ መሆኑ በጣም ግልፅ ነው፡፡

ነገር ግን ሁሉም ሕጎች በአንድ ሀገር የሚታወጁት በፓርላማ ወይም በሌላ በተመረጠ አካል ብቻ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡ ሕግ የማውጣት ስልጣን በውክልና ሌሎች አካላት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዋናነት ለክልላዊ ወይም አካባቢያዊ አካላት ወይም በጥቂት ዲሞክራሲያዊ ሀገሮች በፓርላማ ውስጥ ያልተመረጡ ተወካዩች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ዋናው ነገር ሕግ የማውጣት ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎች በሕግ ስር መሆናቸው እና ተገቢ የሕገመንግስት ግንዛቤ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ይህ የሕግ የበላይነት ሥነሥርዓታዊ ባህሪ በተወሰነ መጠን በጥቂትዲሞክራሲያዊ ባልሆኑ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች እውን ሊሆን እንደሚችል አይካድም፡፡ በእነዚህ ሥርዓቶች ፓለቲከኞች ሥልጣናቸውን ሕግን በመጠቀም ሥራ ላይ ያውሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ራሳቸው ብዙ ጊዜ ለህጎቹ ተገዢዎች አይደሉም፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች የአገዛዝ ባህርይን ሊገልጽ የሚችለው የሕግ የባለይነት ሳይሆን በሕግ መግዛት ነው፡፡

ሦስተኛው ገጽታ የሕጉን ይዘት ያመለከታል፡፡ እዚህ ላይ አንገብጋቢው ነጥብየሕግየበላይነት የሰብዓዊ መብት መከበርንመፈለጉ ነው፡፡ይህ አባባል በተለይም የሲቪል እና የፖለቲካዊ መብቶችን በተመለከተ እውነትነት አለው፡፡ የመናገርና የመሰብሰብ ነፃነት ባልተከበረበት የሕግየበላይነት እንዴት ሊሰፍን እንደሚችል ማለም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶችን ጨምሮ ሌሎች ሰብአዊ መብቶችንም ይመለከታል፡፡

የኋለኞቹ ሁለት የሕግ የበላይነት ገጽታዎች ዲሞክራሲያዊ እና ሰብዓዊ መብቶች በራሳቸው ወሳኝ ርዕሶች እንደመሆናቸው መጠን ከዚህ በታች እሱን በሚመለከተው አውድ ሥር ይነሳሉ፡፡ የመመሪያው ቀጣዩ ትኩረት የሕግ የበላይነትን ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነውየሚለው ይሆናል፡፡

ግን ሕግ አውጪው የዜጎች አመኔታ እና ብሎም ህጉ ተገቢነት ሊኖረው እንደሚገባ ሳይዘነጋ ነው፡፡ ይህ አመኔታ ሊመሠረት የሚችለው ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ብቻ ሲሆን በተለይም በምሥጢር ድምጽ በተመረጠ ፓርላማ ወይም ሸንጎ ሊሆን ይችላል፡፡

## 2.2 በብሔራዊ ደረጃ ለሕግ የባለይነት የሚስፈልጉ ሁኔታዎች

### 2.2.1 ሕገ-መንግስታዊነት

*የሕግ የባለይነት መሠረታዊ መመዘኛ ሕገ መንግስታዊነት ሊባል ይችላል፡፡ በሕግ ሥርዓቱ ውስጥ የአስፈጻሚውን፣ የሕግ አውጪውን፣ የህግ ተርጓሚውን ስልጣን የሚያስቀምጥ ሕግ መኖር አለበት፡፡ መሠረታዊ ሕጉ የትኛው የመንግስት አካል እነዚህን ስልጣኞች የመትገበር ሃላፊነት እንዳለውና በአካላቱ እርስ በእርስም ሆነ በአካላቱና በዜጎች ወይም በአካላቱና በሌሎች የግል ተቋማት መካከል እንዴት እነዚህ ሥልጣኖች እንደሚተገበሩ ማስቀመጥ አለበት፡፡*

*ከሁሉ በላይ ይህ ድንጋጌ በእነኚህ ልዩ ልዩ ሥልጣኖች አጠቃቀም ላይ ያለውን ገደብ በአጠቃላይ አገላለጽ ማስቀመጥ አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር ሕገ መንግስት የሕግ ሥርዓቱን መሰረታዊ አወቃቀር፣ ድንጋጌዎች እና ማን የትኛውን ስልጣን እንዴት መተግር እንዳለበት በግልጽ ማቅረብ አለበት፡፡ እንዲህ ያለ ሕገደንብ በሌለበት ሁኔታ መንግሥት ለሕግ የበላይነት ታማኝ ፤መሆን አለመሆኑን በምክኒያታዊነትና እርግጠኛነት መለካት አይቻልም፡፡*

*ይህ የመሠረታዊ ሕግ ስብስብ ብዙ ጊዜ ሥርዓቱን በሚያሟላ ሰነድተጠቃልሎተጽፎ የሚቀመጥ ሲሆን የዚህ ሰነድ መጠሪያ « ሕገ-መንግስት» ይባላል፡፡*

*የተጻፈ ሕገመንግስት ኖሯቸው በአሳዛኝ ሁኔታ የሚያዘው የማይተገበርእና ሕገመንግሥቱ በተግባር ሥልጣን ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ የማያንጸባርቅ ሀገሮች አሉ፡፡ በእነዚህ መንግስታት የተጻፈ ሕገ-መንግስት ውጪን ከማሳመር ባለፈ ፋይዳ የለውም፡፡*

*ያልተጻፈ ሕገመንግስት ያላቸው መንግስታት እንዳሉ መታወቅም አለበት፡፡ እንዲሁም እንደ እስራኤል ያሉ ሕገመንግስታዊ ባህርይ ያላቸው የተለያዩ ሕጎችና ሰነዶች በቅይጥየሚገኙባቸውም አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሥርዓት ከተፃፈ ሕገ-መንግስት ጋር ተጣምሮም ሊኖር ይችላል፡፡ ፖለቲከኞች ስለሌሎች ሀገሮች ህገ መንግስት ያላቸውን ግንዛቤ መጨመር እንደሚጠበቅባቸው ግልጽነው፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ለአዳዲስ የፓርላማ (የተወካዩች ም/ቤት ተመራጮች) የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጣናዎች ይሠጣሉ፡፡*

### 2.2.2 ለህዝብ ይፋ ማድረግ (ማሣተም) ፣ግልፅነት፣ ወደኃላ

#### *ተመልሶ አለመስራት እና መረጋጋት (አለመዋዠቅ)*

የሕግ ድንጋጌዎች የሰውን ባህርይ ሊገሩ የሚችሉት የሚመለከታቸው ሰዎች ሲጀመር የህጎቹን መኖር (ሕልውና) ካወቁ ብቻ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ህጎች መታወጅ ማለትም ለህዝብ ይፋ መሆን አለባቸው፡

፡

ከዚህም በተጨማሪ ህዝብ ህጎቹን ካልተረዳቸው በስተቀር ሊታዘዝላቸው ስለማይችልህጎቹበበቂ ሁኔታ ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

ህጎች ከወጡ ጊዜ አንስቶ ወደ ፊት ያለውን እንጂ ወደ ኋላ ያለፈውን ሊገዙ የማይገባ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነጥብ ነው፡፡ ይህ ህግ ወደ ኋላ እንዳይሰራ የሚከለክል መርህ በተለይ ለወንጀል ህግ በጣም በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ ነጥብ የእ.ኤ.አ በ1948 በተዘጋጀው የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ላይ የተካተተውም

ለዚህ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2 ‹‹ማናቸውም ሰው ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ በብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ሕግ ወንጀል ጥፋት ባልነበረ አድራጎት በወንጀል ጥፋት ሊቀጣ አይገባም›› ሲል ይደነግጋል፡፡ አለም አቀፍ እና አህጉራዊ (አከባቢያዊ) የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችም ይህንን መሰረታዊ መብት አፅንተውታል፡፡

ይሁን እንጂ ለዚህ አጠቃላይ መርህ አንድ የታወቀ ልዩ ሁኔታ አለ፡፡ ይህም የተወሰኑ አለም አቀፍ ወንጀሎች የሚያስከትሉት ኃላፊነት ነው፡፡ ይህም በዓለም አቀፍ የሲቭል እና የፖለቲካ መብት ቃል ኪዳን አንቀፅ 15 ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ‹‹ይህ አንቀፅ ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ በመንግስታት ተቀባይነት ባገኘ አጠቃላይ የሕግ መርህ መሰረት በወንጀል የሚያስጠይቅ ጥፋት በማድረግ ወይም ባለማድረግ የሚከሰሱ ወይም የሚቀጡ ሰዎችን አያካትትም›› ተብሎ የተደነገገውን ይመለከታል፡፡ ሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችም ተመሳሳይ አንቀፅ አላቸው፡፡ እ.ኤ.አ በ1998 በወጣው (የሮማ ድንጋጌ ተብሎ በሚጠራው ሥር) የወጣው የዓለም አቀፍ ወንጀል ፍ/ቤት ሥልጣንም እነዚህ ላይ በምሳሌነት ሊጠቀስ ይገባል፡፡

ከዚህ ሌላ ህጎችና በተለይም ህገ መንግስታት በጊዜ ሂደት የተረጋጉ ሊሆኑይገባል፡፡ በየጊዜው የሚለወጡና የሚሻሻሉ ሊሆን አይገባም፡፡ ህጎች አሁንም አሁንምየሚለወጡ ከሆኑ ለመከታተል ያስቸግራል፡፡ለውጦች ሲበዙ ስለህጉ ይዘት ዘላቂ የሆነ መወዛገብ ይፈጠራል፡፡ የረጅም ጊዜ መርሀግብር የሚጠይቁ ሥራዎችን መስራት የማይችል ይሆናል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ንግድ ለማቋቋም ካሰበ ግብርና የግብር እፎይታ የሚመለከቱ ሕጎች ለተወሰነ ጊዜ ፀንተውየሚቆዩ መሆን አለመሆኑን ማወቅ የግድ ይላል፡፡

መረጋጋት ስንል አንፃራዊ ነው፡፡ ህጎች ቢያንስ ለምን ያህል ጊዜ ፀንተው ሊኖሩ እንደሚገባ ለመወሰን ያስቸግራል፡፡ በተጨማሪም መረጋጋት ለአንዳንድ የህግ አይነቶች ከሌሎች ይልቅ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለማለት ሚቻለው በጥንቃቄ ማቀድ እና እሩቅ አስቦ መወሰንን የሚጠይቁ ስራዎችን የሚያውኩ ህጎች የአጭር ጊዜ እቅድን የሚጠይቅ ስራዎችን ከሚያውኩ ሕጎች ይልቅ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንተው ሊቆዩ ይገባል፡፡

የአውሮፓ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ባንድ በታወቀ ጉዳይ (ስንደይ ታይምስ እና የእንግሊዝ መንግስት እ.አ.አ በ1979 በተከራከሩበት) በሰጠው ውሳኔ አብዛኞዎቹን የተነሱትን ሁኔታዎች ባጭሩ አስቀምጧቸዋል፡፡ ህጎቹ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ (በህዝብ ሊገኙ የሚችሉ) መሆን አለባቸው፡፡ ዜጎች አንድን ጉዳይ በሚመለከት ከሁኔታዎች አንፃር ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጎችን በበቂ ማወቅ በሚያስችላቸው ሁኔታ መረጃ ማግኘት (መጠቆም) አለባቸው፡፡ አንድ የሕግ ድንጋጌአንድን ዜጋ ባህሪውን መግራት በሚያስችለው በበቂ እና ግልፅ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር እንደ ሕግ ሊቆጠር አይችልም፡፡ ዜጋው (አስፈላጊ ከሆነ ተገቢ የህግ ምክር ተሰጥቶትም ቢሆን) አንድ ድርጊት ሊያስከትል የሚችለውን የሕግ ውጤት ከሁኔታዎቹ አንፃር በቂ ነው ተብሎ በሚገመት ደረጃ ማወቅ (መገመት) መቻል አለበት፡፡

### 2.2.3. የፓርላማዎች ልዩ ኃላፊነት

ፕርላማዎች (የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች) ከላይ የተጠቀሱትን መርሖዎች ስራ ላይ የማዋል ልዩ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ታትመው መሰራጨታቸውን እና ግልጽና የማይዋዥቁ (የተረጋጉ) መሆናቸውን መቆጣጠር አለባቸው፡፡ ይህ ጥንቃቄበተሞላበት ሁኔታ መካከታተልን ይጠይቃል፡፡ ግልፅ መሆን አለበት ስንል አሻሚ ያልሆኑ ቃላትን መጠቀምን ብቻ የሚጠይቅ አይደለም፡፡ በተጨማሪምበነባርና በአዳዲስ ሕጎች መካከል ወጥነትን (መጣጣምን) የሚጠይቅ ነው፡፡ አዳዲስ ሕጎች የቱንም ያህል ግልፅ በሆነ ሁኔታ ቢረቀቁ ከነባር ሕጎች ጋር ሲተያዩ ለተመሳሳይ ቃላት የተለያየ ፍቺ ከሰጡ ለያደናግሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ብዙ ሕግ ማውጣት እና ተመሳሳይ ጉዳይን የሚገዙ ተደራራቢ ሕጎችን ማብዛት ዜጎችን በማደናገር ግልፅነትን ሊሸረሽር ይችላል፡፡

ሕጎች ግልፅነትን ሊላበሱ የሚችሉት ሕግ አርቃቂ ባለሙያዎቹ ሕግ የማርቀቅበቂ እውቀት እና ክህሎት ሲኖራቸው ነው፡፡ ስራው በፓርላማ አባላት አማካኝነት ሊሰራ ቢችልም አብዛኛውን ግዜ የሚሰራው በፓርላማ ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቶች ውስጥ በሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች አማካኝነት ነው፡፡ የሕግ የበላይነት ሰፍኖ ማየት ለሚፈልግ ስርዓት አርቃቂ ባለሙያዎቹ በቂ ስልጠና የወሰዱ እና እውቀት (ክህሎት) ያላቸው መሆናቸው በጣም ይጠቅማል፡፡ይህን በተመለከተ የፓርላማዎች ህብረት ተጨማሪ መረጃ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

እላይ ሕግ ወደ ኋላ ሊሰራ እንደማይገባ የተነሳው በዋናነት ሕግ ተርጋሚውንና ሕግ አስፈፃሚውን (በተለይም ዓቃቤ ሕግን) የሚመለከት ቢሆንም ፓርላዎችም (የሕዝብ ተወካይ ም/ቤቶች) እዚህ ላይ ኃላፊነት አለባቸው ፡፡ ይህ መርሕ ይበልጥ አንገብጋቢ ከሚሆንበት ከወንጀል ሕግ ጋር በተገናኘ ዳኞችና ዐቃቢያነ ሕግ ብዙ ጊዜ ከረጅም ዓመት በፊት የተረቀቁ እና ወቅታዊውን ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ የማይሸፈኑ ድንጋጌዎች የሚያጋጥሟቸውሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ፓርላማዎች በተለይ የቆዩ ህጎች ቃላት ወቅቱ ከሚጠይቀው ደረጃ እና ከጊዜው የሕዝቡ፣ የሕግ አውጪው እና የሕግ ባለሞያዎች አስተሳሰብ ጋር የሚሄድ መሆኑን መፈተሸና ማረምብሎም ችግሩን መቅረፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሕግ ወደ ኋላ እንዳሰራ መከልከሉ ሁልጊዜ ሕጋችንን እንድንፈትሽና መሻሻል ያለበትን በወቅቱ እንድናርም ስለሚያደርገን የራሱ የሆነ ጥቅም አለው፡፡

ሕግ አስፈፃሚውም እንዲሁ የሕጋዊነትን መርሕ ሥራ ላይ በማዋል በኩል የራሱ የሆነ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የመንግስት የአስፈፃሚው አካል እያንዳንዱ ሕግ ሰላለበት ወቅታዊ ሁኔታ ሕጉ ለሚመለከታቸው የሕብረተሰብ ክፍል በየጊዜው በሚመጥናቸው የቋንቋ አገላለጽ የሚያሳውቃቸው ከሆነ ሕጎችን ለሕዝብ የማዳረስ እና ግልፅ የማድረግ ስራ በተሳካ ሁኔታ ይፈጸማል፡፡ እዚህ ላይ ድረገድ ጉልህ ሚና አለው፡፡ ድረገጽንም ሆነ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃውን ለሙያ ማህበራት፣ ለጠበቆች ማህበራት፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ ለነፃ የሕግ አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች ወዘተ. ማስተላለፍ ይጠቅማል፡፡

### 2.2.4. የመወሰን ስልጣን

የሕግ የበላይነት መርሕ መንግስት በተቻለ መጠን በአጠቃላይ እና አስቀድመው ለሕዝብ በበቂ ሁኔታ በተገለጹ ሕጎች መሰረት ስልጣኑን ስራ ላይ እንዲያውል ያዛል፡፡ ነገር ግን መንግስት ሁሉንም ውሳኔ አስቀድሞ በወጣ ሕግ ሊወስን አይችልም፡፡ በአስተዳደር ውስጥ በመሰለው መወሰን እና በትእዛዝ መሥራት ሊቀር የማይችል ነገር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሕግ የበላይነትን መርህ ለሚሟላት ሲባል የማዘዝና በመሰለው የመወሰን ሥልጣን ጠቅለል (ሰፋ ባለ አነጋገር) በተቀመጡ ድንጋጌዎች መገራት አለበት፡፡

በተጨማሪም የመንግስት የአስፈጻሚው ክፍል በመሰለው የመሥራት (የመወሰን) ሥልጣኑን በሆነው ባልሆነው መጠቀም የለበትም፡፡ በተለይ የሀገር ደህንነትን የሚያሰጉ ጉዳዮች በምሥጢር መያዝ ያለባቸው እና አንዳንዴም የተወሰኑ ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ (ዲሞክራሲያዊ) መብቶችን በተወሰነ ደረጃ መገደብን የሚጠይቁ ከመሆናቸው አንጻር ይህ በጣም አሳሳቢ ነጥብ ነው፡፡ የህግ የበላይነት አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ጠቃሚ ዓላማዎችና ግቦች ጋር ተመዛዝኖ ሊሸራረፍ የሚችል ሲሆን ይህ ግን በቅን ልቦና መደረግ ያለበት ነው፡፡

መረጃ የማግኘት መብትን የሚመለከቱ ሕጎችና ሕጎቹ የሚፈጸሙበት ሁኔታ ይህንን ለማመዛዘን ጠቃሚ ከመሆናቸውም በላይ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤቶች ፍርዶች እና የዓለማቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ተቆጣጣሪ አካላት መመሪያዎችም ይረዳሉ፡፡

### 2.2.5. የስልጣን ክፍፍል

በሕግ አስፈፃሚው፣ በሕግ ተርጓሚው እና በሕግ አውጪው መካከል ልዩነት እንዲኖር የሕግ የበላይነት መርህ ያስገድዳል፡፡ ይህም ማለት የአስፈፃሚው የመንግስት አካል፣የፓርላማውና የፍርድ ቤቶች መለያየት ብቻ ሳይሆን ግለሰቦች በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የአንዱ ብቻ እንጂ ደርበው የሁለቱም ሆነ የሶስቱም አባላት እንዳይሆኑ ይጠበቃል፡፡ ለምሣሌ አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዳኛ ሆኖ ማገልገል አይችልም፡፡

በእርግጥ ትክክለኛ የሆነ የስልጣን ክፍፍል (በእነዚህ ተቋማት መካከል) ተደርጎ ያውቃል ለማለት ያስቸግራል፡፡ በሁሉም ሃገራት ሁለት ስልጣን ያለቸው ተቋማት አሉ፡፡ አስፈፃሚው አካል ሕጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ሲያወጣ ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪም የተጻፈ ሕግ ባላቸውም ሆነ በሌላቸው ሀገራት የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ሕጉ እንዴት መተርጎምና መተግበር እንዳለበት የሚደነገጉ ሕግጋት ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ይህም ዳኞች ፍርድ ሰሰጡ በብሔራዊ ደረጃ ሕጎች እንዲዳብሩ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ብዙ ሃገሮች ግለሰቦች የሁለት ተቋማት አባላት እንዲሆኑ ይፈቅዳሉ፡፡ ለምሳሌ በብሪታንያአንድ ሚኒስቴር የፓርላማ አባል የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ በእርግጥ በብዙ ሀገሮች ያለው ሁኔታ ጥብቅ የሆነ የሥልጣን ክፍፍልን የሚያመለክት ሳይሆን አንደኛው አካል ሌላኛውን የሚቆጣጠርበትንና የሚያስተካክልበትን መንገድ የሚያሳይ ነው፡፡ በእነዚህ አገራት ሥልጣን በተለያዩ አካላትና ግለሰቦች መካከል የሚከፋፈለው አንደኛው አካል ሌላኛውን እንዲቆጣጠረው በማድረግ አንድ

ግለሰብ ወይም ተቋም ለብቻው ፍፀም የሆነ ሥልጣን እንዳይኖረው ለመከላከል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ፓርላማዎች የሕግ አስፈፃሚዎችን ስራ ይከታተላሉ፡፡

ትክክለኛ የሆኑ ቁጥጥሮችንና ክትትሎችን የተከተለ አሰራር ለሕግ የበላይነት መስፈን ወሳኝ ነው፡፡ የሕግ አስፈፃሚነትን እና የሕግ አውጪውነትን ስራ አንድ ተቋም ወይም አንድ ግለሰብ ደርቦ ከያዘ ከሕግ የበላይነት ግቦች መካከል አንዱ የሆነው ማለትም ሥልጣንን መገደብ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 2.2.6. ፍርድ ቤቶች

የሕግ የበላይነት እንዲኖር ወሳኙ ወገናዊ ያልሆኑ እና ነፃ የሆኑ አለመግባባቶችን በመፍታት ሕግን ለማስከበር ብቁ የሆኑ ፍ/ቤቶች መኖር ነው፡፡

በማንኛውም ማህረሰብ ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ አንዳንዶቹ በመንግስት እና በዜጎች መካከል ይሆናሉ፡፡ ሌሎቹ በግለሰቦች መካከል ወይም በተቋማት መካከል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አንዳንድ ግጭቶች ፍሬ ነገርን (እውነታን) የተመረኮዙ ናቸው፡፡ ፓሊስ አንድን ሰው በአድማ ተካፍለሃል ብሎ ሲጠይቀው ግለሰቡ ሊክድ ይችላል፡፡ አንዲት ሴት ጎረቤቷ ገንዘብ ተበድሮ አልከፈለኝም ስትል ጎረቤቷ ሊክዳት ይችላል፡፡

ሌሎች ግጭቶች ደግሞ በሕግ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በጋዜጣ ላይ ባለቤቱ በዚህን ያህል ዋጋ ለመሸጥ ስለጋበዘ እና እኔ እንደተስማማሁ በቃል ስለገለጽኩለት አንድን ቤት ሕጋዊ በሆነ ውል ገዝቻለሁ ሊል ይችላል፡፡ ባለቤቱ ደግሞ ይህ ለመዋዋል ሳይሆን ድርድር ለመጀመር የተሰናዳ ማስታወቂያ ብቻ ስለሆነ የመሸጥ ግዴታ የለብኝም ብሎ ሊከራከር ይችላል፡፡

### ግጭቶች በሕጉ መሰረት መዳኘት አለባቸው

ከላይ እንደተጠቀሱት ያሉ ግጭቶች በሕግ መሰረት መዳኘት አለባቸው፡፡ አንድ ውሳኔ እውነታንና ሕግን ተመርኩዞ መሰጠት አለበት፡፡ እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች ከሌሉ አለመግባባቱ ይቀጥላል፤ ወይ በሌላ መንገድ ያለዚያም ከባሰበት በሀይል ይፈታል፡፡

በተጨማሪም ባለስልጣናት ሆኑ ዜጎች ሕጉን እንዲያከብሩ ከተፈለገ ሕጉ እንዴት መተርጎም እንዳለበት እና ከእውነታው ጋር ተገናዝቦ እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንዳለበት ማወቅ አለባቸው፡፡ ለዚህም ብቃት ያለው አካል (የበላይ ፍ/ቤት) የሚሰጠው ውሳኔ ይረዳል፡፡ ይህም በአንድ ጉዳይ ውስጥ ያሉትን ግጭቶችን ከመፍታት አልፎ ባለስልጣናት እና ዜጎች ሕጉን እንዲረዱትና እንዲታዘዙት ያስችላቸዋል፡፡

### ነፃነት

ውሳኔዎች በ3ኛ ወገን፣ በዳኛ ወይም በፍ/ቤት መሰጠት አለባቸው፡፡ የዳኝነት አካላት ከውጪ ተፅዕኖ ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ በሕግና በሕጉ ብቻ ውሳኔ መስጠት አለባቸው፡፡ ይህም ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ከመንግስት ነፃ ሊሆኑ ይገባል ፡፡ ውሳኔያቸው ከገዢዎች ተፅዕኖ ነፃ መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ዳኞች ለሙያ ስነምግባር እና ክብር ተገዢ እና ተገቢነት ያለው ፍርድ ለመስጠት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፡፡

ይህ ነፃነት በዳኞች አሿሿም፣በስራ ባሕርይ፣ በስራ ዋስትና እና በደመወዝ አከፋፈል ስርዓቶችና ሕጎች ከመንግስት ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ መረጋገጥ እና መጎልበት አለበት፡፡

**አለማዳላት**

የዳኛ ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ መሆን ማለት በሁለተኛ ደረጃ ዳኛው ወይም ዳኛዋ ለየትኛውም ወገን አለማዳላታቸውን ያካትታል፡፡ ዳኛው የሚያዳላ መሆኑን ተከራካሪ ወገኖች ከጠረጠሩ ሊሚገቱት መብቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህም ዳኛውን ጉዳዩን እንዳያይ ማስነሳት ይችላል፡፡ ዳኞች ከተከራካሪ ወገኞች ከአንደኛው ጋር የዝምድና ወይም ሌላ ዓይነት ትስስር ካላቸው ከጉዳዩ ለመነሳት ሙብት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የዳኞችን ነፃነት ወይም ከአድልዎ ነፃ መሆንን በከፍተኛ ደረጃ ከሚፈታተኑ ነገሮች አንዱጉቦኝነት (ሙስና) ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ለዳኞች በቂ ደመወዝ እና የስራ ዋስትና ማመቻቸት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ዳኞች የሙያውን ሥነምግባር እና ክብር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

**የሙያ ስነምግባር**

ፍትሕን በዕኩልነት ለሁሉም ከውጭ ተፅዕኖ በጸዳ ሁኔታ ለማዳረስ ትክክለኛ ሕጎችን ማውጣት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ሁሉም ወገኞች ክርክርን ግጭትን በመፍታት በኩል ጥሩ የሙያ ስነምግባር እና ባሕርይ ሊያሳዩ ይገባል፡፡ ዳኞች በግል ሕይወታቸው ነፃነታቸውንና ከአድልዎ ነፃ መሆናቸውን ለሚፈታተኑ የውጭ ግፊቶች ራሳቸውን ማጋለጥ የለባቸውም፡፡ ዜጎች ዘወትር ሕግ በሚጥሱባቸው (የመጣስ አዝማሚያ በሚያሳዩባቸው) ተራ ጉዳዮች ላይ እንኳ ሕጉን በትክክል መከተል አለባቸው፡፡

ዳኞች ሕጋዊ ቢሆኑም ነገር ግን ተፅዕኖ ውስጥ ሊከቷቸው በሚችሉ ድርጊቶች ውስጥ ከመሳተፍ መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ወደ ሕጋዊ የቁማር መጫወቻ ቦታዎች መሄድ የለባቸውም፡፡ ኢቃቢሕጎችም እንደዚሁ፡ ፡

**የፓለቲከኞች ሚና**

ፖለቲከኞች በይፋ በህዝብ ፊት የህግ ትርጓሚውን ነፃነት መቀበላቸውና ማክበራቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡ ፡ ፓለቲከኞች በፍ/ቤት በመታየት ላይ ያለ ጉዳይን በተመለከተ የሚፈልጉትን ውጤት የሚያንፀበርቅ አስተያየት መስጠት የለባቸውም፡፡ ይህም በዳኞች ወይም በሕዝብ በፍርዱ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ለማድረስ ተብሎ እንዳተደረገ ጫና ሊቆጠር ይችላል፡፡

ፓለቲከኞች አንዳንድ የፍርድ ውጤቶች በትክክል አልተወሰኑም ከማለት ወይም ስለዝርዝር ጉዳዮች ከመተቸት መቆጠብ አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ስለ አንድ ፍርድ ምንም መናገር አይችሉም ማለትአይደለም፡፡ የአንድ ወይም የተለያዩ ፍርዶች ውጤቶች ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የማይሄዱ ከሆነ አዳዲስ ሕጎች እዲወጡ ወይም እንዲሻሻሉ ፍለጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በጥቅሉ አስተያየት ከመስጠት ውጪ ጉዳዮችን ለይተው ጠቅሰው ዳኞች በትክክል አልወሰኑም ብለው መተቸት ጨርሶ የለባቸውም፡፡

በእርግጥ ፍርዶቹ ሙሉ በሙሉ በሕጉ መሰረት የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ሲሆን ሃላፊነቱን መውሰድ ያለበት ሕግ አውጪው አካል ነው፡፡

ፓለቲከኞች ስለዳኞች አቀጣጠር ሂደትና መስፈርቶች በሚናገሩበት ጊዜ መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ፍርድ በትክክል አልተወሰነም፤ ያም በመሆኑ ጉዳዩን ያየውን ዳኛ የስራ ዋስትና መንሳት እና ከስራው እንዲባርር ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ አስተያየት መስጠት ተገቢ አይደለም ፡፡

ነገር ግን የዳኞች ነፃነት እና ከአድልዎ ነፃ መሆንን በማይነካ መልኩ ስለዳኞች የሥራ ዋስትና መወያየት እንደሚችሉ አይካድም፡፡

ሆኖም ፓርላማዎች የፍትሕ ስርዓቱ በትክክለኛ መንገድ እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ የሕግ አስፈፃሚውን እና ፍርድ ቤቶችን መከታተል አለባቸው፡፡ ይህ በዳኞች ነፃነት ጣልቃ መግባት አይደለም፡፡

**ፍርድ ቤቶች ክፍት መሆን አለባቸው**

ፍርድ ቤቶች ለማንኛውም ዜጋ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ በጣም ውድ ውስብስብ ወይም አስቸጋሪ ከመሆናቸው የተነሳ ሰዎች ጉዳያቸውን ፍ/ቤት ከማቅረብ እንዳይቆጠቡ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በህግ የበላይነት በሚመራ ሕብረተሰብ ውስጥ የፍትህተደራሽነት ወሳኝ ነው፡፡

ይህም ማለት በመጀመሪያ አንድን ጉዳይ ፍ/ቤት እንዲታይ መሟላት ያባቸው መስፈርቶች በጣም ከባድ እና ጥብቅ መሆን የለባቸውም፡፡ በጉዳዮች መብዛት ፍ/ቤቶች በጣም እንዳይጨናነቁ እና የፍርድ ሥርዓቱ እንዳይዛባ አንድንድ ገዳቦች መጣላቸው አይቀርም፡፡ ግን ማናቸውም ገደቦች ሲጣሉ ተቀባይነት ያላቸው ዓላማዎችን ግብ ማድረግ እና ግቦቹን ለመምታት የግድ አስፈላጊ መሆን አለባቸው፡፡

ለምሳሌ አንዳንድ ወንጅሎች ከባድ ቅጣት የሚያስከትሉ ከሆነ እና የሕግ ስነ ሥርዓቱ ውስብስብ ከሆነ ተጠርጣሪዎቹ በጠበቆች ሊወከሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዳኞች ብቻ ሊያልቁ በሚችሉ ጥቃቅን ጉዳዩች ጠበቆችን መወከል የሚያስፈልግ አይመስልም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የዳኝነት ክፍያዎች ተመጣጣኝ እና ዋጋውን ለመክፈል አቅም ለሌላቸው ደግሞ ድጎማዎች መደረግ አለባቸው፡፡ለጠበቆች ለመክፈል ለማይችሉ ደግሞ በተመሳሳይ የነፃ የጥብቅና አገልግሎት መኖር አለበት፡፡

ለምሳሌ በአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት አንቀጽ 6 መሰረት ሰዎች በወንጀል ጉዳዮች ነፃ የሕግ አገልግሎት መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡ በኤይሪ እና አየርላንድ መካከል በተደረገ ክርክር በአንዳንድ ሁኔታዎች መንግስታት በፍትሐብሔር ጉዳዮችም ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ማዘጋጀት እንዳለባቸው የአዉሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍ/ቤት ገዢ ፍርድ ሰጥቷል ፡፡ በሌላ በኩልም ወደ ፍርድ ቤት የሚደረጉ ጉዞዎች በጣም የራቁ መሆን የለባቸውም፡፡

**የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል**

የፍ/ቤት ክርክሮች ረጅም ጊዜ ሳይወስዱ ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ ውሳኔ ሊያገኙ ይገባል፡፡ የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የተለመደ አባባልም ጥሩ ዕይታ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ፓርላማዎች ፍርዶች በትክክለኛው ጊዜ ሊሰጡ የማችሉበት አሰራር በፍትህ ስርዓቱ መዘርጋቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**የስነ ሥርዓት ሕጎች ፍትሃዊ መሆን አለባቸው**

ከዚህ ሌላ በፍ/ቤቶች የሚተገበሩ የስነ ሥርዓት ሕጎች ትክክለኛ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ክሶች በግልፅ በሕዝብ ፊት በይፋ መሰማት አለባቸው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ከፈለጉ በውክልና መከራከር፣ ክርክራቸውን ለማቅረብ በቂ የዝግጅት ጊዜ ማግኘት፣ ሌላው ወገን ላቀረበው ክርክር መልስ መስጠት፣ ጉዳያቸው በበላይ የሕግ አካል በይግባኝ እንዲታይ ማድረግ መቻል አለባቸው፡፡

## 2.2.7. አማራጭ ሙግት መፍቻዎች

የሕግ የበላይነት ግጭቶች ከፍርድ ቤት ውጭ በሌሎች መንገዶች የሚፈቱበትንም ያካትታል፡፡ እነዚህ አማራጭ መግት መፍቻ መንገዶች በከፍተኛ ደረጃ ተመራጭ የሚሆኑበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ እነዚህ የሽምግልናና የድርድርን ጨምሮ ሌሎች መንገዶችን ያካትታሉ፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤት መሰል የሆኑ እንደ ህዝብ እንባ ጠባቂ ያሉ ተቋማትም እንደ በመንግስት ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ያሉ አቤቱታዎችን ሊያጣሩ ይችላሉ፡፡

እነዚህ ግጭት አፈታት ዘዴዎች ብዙ ጥቅሞች አሏቸው፡፡ ከወጪ፣ ብዙ ከመጓዝ (ከርቀት)፣ ተፈፃሚነት ከማግኘት፣ ፍርድ ቤት ላይ ያለ ጫናንም ከመቀነስ አንጻር ጥሩ ዘዴዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በፍርድ መዋቅር ውስጥ ቀለል ባለ ሥነ ሥርዓት አንደ አነስተኛ ጉዳዮችን የሚያዩ ትናንሽ ፍ/ቤቶችን፣ እንዲሁም አስገዳጅ የእርቅ ስነ ሥርዓቶችን ማቋቋም ይቻላል፡፡

በፍ/ቤትም ሆነ ከፍ/ቤት ውጪእንደ እነዚህ አይነቶች የሙግት አፈታት አማራጭ ዘዴዎች፣የአፈታቱን ሂደት፣ ጥራትና ውጤታማነት ከማሳደጋቸው አንፃር ለሕግ የበላይነት መጎልበት አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ይህ እንዲሳካ ግን እነዚህ ዘዴዎች (ተቋማት) ለሁሉም ወገኖች አገልግሎት የሚሰጡ፣ በትክክል የመዳኘት መብትን የሚያሰፍኑና በነፃነትና ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንገድ የሚሰሩ መሆን አለባቸው፡፡

ከዚህ አንፃር በብዙ ሃገራት ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ተቋማት ከግለሰቦች የሚመጡ አቤቱታዎችን (ስሞታዎችን)ተቀብሎ የማጣራት መብት አላቸው፡፡ አስፈላጊ ሲሆንም አቤቱታ አቅራቢዎቹን ስሞታ ከቀረበበት መንግስታዊ ተቋም ጋር በምሥጢር የማደራደር ስራ ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም የሰብዓዊ መብት ተቋሞቱ ያሉትን ሁኔታዎች ለፓርላማ በማቅረብ (በማሳወቅ) በሃገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ እንዲሻሻል ወይም የተሻሉ ሕጎች እንዲወጡ ግፊት ያደረጋሉ፡፡

የብሔራዊ የሰብአዊ መብት ተቋማትን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 48/134 (እኤአ ዲሴምበር 20/1993 ወይም ታህሳስ 11/1985 ዓ.ም የወጣዉ) የፓርስ መርሖዎች ላይ ተጨማሪ መመሪያዎችን ማየት ይቻላል፡፡

### 2.2.8. ሌሎች ውሳኔ ሰጪ አካላት

ከፍ/ቤቶች በተጨማሪ ሕግን ተጠቅመው ውሳኔ የሚሰጡ አስተዳደሮች ባለስልጣናትና ተቋማት አሉ፡፡

ከሚኒስትሮች ጀምሮ እስከ አቃቤ ሕጎች፣ ፓሊስ፣ የግብር ሰብሳቢ፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት

እና በየደረጃው ያሉ አስተዳደሮች ሕጎችን መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የእነዚህ አካላት ውሳኔዎች በዜጎች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ የሕግ የበላይነት ሊሰፍንየሚችለው እነዚህ አካላት በትክክል ሕግን ተመርኩዘው ሲሰሩ ነው፡፡

### 2.2.9. በቂ የሆነ አተገባበር

የህግ የበላይነት ሲባል መንግስታዊ ስልጣንን በሕግ መግራት ማለት ነው፡፡ ይህም ስልጣንን መጠቀም የሚችሉት ህጋዊ ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ሆነው የሚሰሩትም በህግ መሰረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህጎች በጥንቃቄ እንዲተገበሩ እና ሲሰራባቸውእንዲታይ ይጠይቃል፡፡ ባለስልጣናት ህግን አንድም እንዲያከብሩት በሌላ በኩልም እንዲያስከብሩት ይጠይቃል፡፡ ዜጎች ሕግን ማክበር ካለባቸው በእርግጥም ህጉ በትክክል እየተከበረ እንደሆነ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ዜጎች ሕጎች የማይከበሩ መሆናቸውን ከአውቁና ባለስልጣኖችናግለሰቦች ከተፃፈው ሕግ ውጪ ያሉ ልማዳዊ አሰራሮችን የሚከተሉ ከሆነ ሕጎችን እንዲያከብሩ ሊጠበቅባቸው አይችልም፡፡ ስርዓት አልበኝነትና ሕግ መጣስ ከተስፋፋም በሕጋዊ ስርዓቱ ላይ አመኔታ እንዳይኖርና ለሕጉ ግድ የለሽ መሆንን ያስከትላል፡፡

ነፃ ፍርድ ቤት በሕጎች እና በዜጎች የዕለት ተዕለት ተግባር (ባህርይ) መሃከል ጥምረት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

በተለይ ደግሞ አስፈፃሚው የመንግስት አካል ከስልጣኑ በላይ እንዳይሰራ ይቆጣጠራል፡፡

ሁሉም ተቋማትና ሠራተኞቻቸው የሕግን የበላይነት አስፈላጊነት እና ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ህጉን የማያውቁት ከሆነ በስራ ላይ ማዋል አይችሉም፡፡ እንዲሁም ስለህግ የበላይነት ምንነትና አስፈላጊነት ግንዛቤ ከሌላቸው ለህግ የበላይነት ሊቆሙአይችሉም፡፡በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የመንግስት አካላት የሕግ የበላይነትን በተመለከተ ተገቢው መረጃ እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን በስራቸው ላይ ስለሚያስከትለው ውጤትም ስልጠና እንዲወስዱ ጥረት ማድረግ የግድ ነው፡፡

ፓርላማም ይህን በተመለከተ አመቺ በሆነ ዘዴ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

### 2.2.10 ጥንቃቄዎች

ለሕግ የበላይነት ሥርዓት መስፈን የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በስፋት ማየት ይቻላል:: ነገር ግን ለዚህ

ፅሁፍ (መመሪያ) በቂ የሆኑት ብቻ ቀጥሎ ተጠቅሰዋል፡፡

**ጥርት ያሉና የማያወላዱ መስፈርቶች የሉም**

ቁጥር ያሉና የማያወላዱ መስፈርቶችን ለሕግ የበላይነት ማውጣት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ ሕጎች ለሚመለከታቸው ዜጎች ግልፅ መሆን አለባቸው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ግን ፍፁም የሆነ ግልፅነትን ማስፈን አስቸጋሪ ነው፡፡

ሲጀመር ቃላት በባህሪያቸው አሻሚና ለትርጉም የተጋለጡ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ የመናፈሻ ቦታ ተሸከርካሪዎች ማቆም ክልክል መሆኑን የሚገልፅ ሕግ ካለ ተሽከርካሪ የሚለው ቃል መኪኖችን፣ የሞተር ሳይክሎችንና ብስክሌቶችን የሚመለከት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ቃሉ እንደ ስኬት መጫወቻዎችን (መንሸራተቻዎች) የመሳሰሉ ዕቃዎችን ስለመጨመሩ ግልፅ አይደለም፡፡ ምንም አንኳን ሁሉም ቃላት አንድ መሰረታዊ የሆነ ትርጉም ቢኖራቸውም ሁል ጊዜ ግን አሻሚ መሆናቸው አይቀርም፡፡

ምንም እንኳን ሕግ ሲፃፍ ቃላትን በመደበኛ ፍቺያቸው መጠቀም ቢኖርበትም ግልፅ እንዲሆኑ ሲባል በተወሰነ መልኩ ለየት ያለ (ሙያዊ) ትርጉም መያዛቸው አይቀርም፡፡ አንዳንድ ህጎች ሆን ብለው ሰፊና አሻሚ ትርጉም ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑት በሕገ መንግስቶች ውስጥ ያሉ የሰብዓዊ መብት ሕጎችና አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የጉዳት ካሳና የውል ሕጎች ውስጥ ያሉ የርትዕና የማቻቻያ ድንጋጌዎች አሻሚ ትርጉም አላቸው፡፡

ሆኖም የቃላት አሻሚነት ግልፅነትን አስኪያሳጣ ድረስ መለጠጥ የለበትም፡፡ዜጎችና ባለስልጣኖች ዋና ዋና ግዴታዎቻቸውንና መብቶቻቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ይቻላል፡፡ በምን ያህል ደረጃ የአገሮች የህግ ስርዓቶች የሕግ የበላይነት መስፈርትን ያሟላሉ የሚለው የሚዛን (የአለካክ) ጉዳይ አንፃራዊና አከራካሪ ነው፡፡

**አጠቃላይ ደንብ**

ሌላው ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ጉዳይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች የአጠቃላይ መመሪያነት ባሕርይ የተላበሱ መሆናቸው ነው፡፡ ፍሬያማ እንዲሆኑ መስፈርቶቹ የበለጠ በዝርዝር ታይተው እና ጎልብተው ወደ ህጎች (ደንቦች) መለወጥ ኖርባቸዋል፡፡ የአጠቃላይ መመሪያነት ባሕርይ ብቻ ያላቸው ከሆኑ ብዙም አያራምዱም፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ አማራጮች መታየት አለባቸው፡፡

ለምሳሌ ፡ በአንዳንድ የሕግ ስርዓቶች ተራ (የሕግ ባለሞያ ያልሆኑ) ሰዎች በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ክርክሮች በዳኝነት ሰጭነት ተሳታፊ ሲሆኑ በሌሎች ግን አይሳተፉም፡፡ ያም ሆነ ይህ ዳኝነት ነፃና ገለልተኛ የክርክር አፈታት ሂደትና የትክክለኛ ችሎትን መስፈርቶች እንዲያሟላ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል ብዙዎቹ የሕግ ሥርዓቶች ለፍ/ቤቶች ሕግ አውጭው አካል የሚያወጣቸውን ሕጎች ከህገ መንግሥቱ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን የሚመረምሩበት ሥልጣን የሰጧቸው ሲሆን ሌሎች የሕግ ሥርዓቶች ግን የላቸውም፡፡ የሆነው ሆኖ በሁለቱም የሕግ ሥርዓት ዓይነቶች የሚወጡት ሕጎች ሕግ መንግስቱን የማይፃረሩ መሆናቸውን የሚከታተል አሰራር ሊኖር ይችላል፡፡

በአንዳንድ ሕጋዊ ሥርዓቶች አቃቢ ሕጎች ማስረጃ እስካለ ድረስ ማንኛውንም ወንጀል (ጥፋት) የመክሰስ ግዴታ ሲኖርባቸው በሌሎች ደግሞ አመዛዝነው ያለመክሰስ ሥልጣን አላቸው፡፡ ነገር ግን በሁለቱም ሥርዓቶች የወንጀል ሕጉ ተፈጻሚነት በቂ እና ተገማች (በሕግ እንጂ በዘፈቀደ የማይነዳ) ሊሆን ይችላል፡፡

**ለሁሉም የሚሆን የተሟላ መፍትሄ ስላለመኖሩ**

መስፈርቶቹ እንዴት ይሟሉ ለሚለው ጥያቄ አንድ ብቻ እና ፍጹማዊ የሆነ መልስ (መንገድ) የለም፡፡

በአንጻሩ እነዚህን መስፈርቶች ለሟሟላት ብዙ መንገዶች አሉ፡፡ በሕግጋታቸውና በሕግ ተቋሞቻቸው ዓይነቶች የሚለያዩ የሕግ ሥርዓቶች መስፈርቶቹን እኩል በሆነ ሁኔታ ማሟላት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የህግ የበላይነትን በአለም ላይ ለማስፈን መፍትሔው አንድ ብቻ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡

በተጨማሪምይህ ማንኛውም ፖለቲከኛ (ባለስልጣን) የራሱ ሥርዓት ብቻ የሕግ የበላይነትን እንደሚያሰፍን ማሰብ እንደሌለበት ያስገነዝባል፡፡ በሀገሮች መካከል የሕግ ትብብር ከተፈለገ እና በሀገሮቹ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ከታሰበ እንደዚህ ዓይነት አመለካከት መወገድ አለበት፡፡

**ንጽጽራዊነትን በተመለከተ ጥንቃቄ ስለማስፈለጉ**

እዚህ ላይ ግን የተለያዩ የሕግ ሥርዓቶችን በምናነጻጽርበት ጊዜ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ጥቂት የሕግ ሥርዓቶች ለሕግ የበላይነት መኖር አስፈላጊ የሆኑ መርሆዎችን ይጥሳሉ፡፡ ዳኞች በቀጥታ በስራ አስፈጻሚው የመንግሥት አካል እንደተፈለገ የሚሾሙ እና የሚሻሩ ከሆነ የሕግ የበላይነት አይከበርም፡፡ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው ለሳምንታት ፍ/ቤት ሳይቀርቡ በእስር ከቆዩ የሕግ የበላይነት እየተጣሰ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ዜጎችን በተመለከተ በመንግሥት የሚተላለፉ ውሣኔዎች በፍ/ቤቶች በይግባኝ የማይታዩ እና ምርመራ የማይደረግባቸው ከሆነ የሕግ የበላይነት የለም ማለት ነው፡፡

## 2.3. በሀገር ደረጃ የሕግ የበላይነት መሥፈን ለምን የግድ ይላል

ባለስልጣናትም ሆኑ ዜጎች በሕግ ሥር መሆናቸው አስፈላጊ የሆነበት ምክንያቱ አንድ ብቻ አይደለም፡፡ የሕግ የበላይነት አላማዎች የተለያዩ ሲሆኑ እርስ በእርሳቸውም የተዛመዱ ናቸው፡፡

### 2.3.1 የሥልጣን ገደብ

በአብዛኛዎቹ ምናልባትም በሁሉም ሀገራት መንግስት በዜጎች ላይ ከፍተኛ ስልጣን አለው፡፡ የመቅጣት ወይምእርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡ ግብሮች ይጥላል፡፡ የገንዘብ ድጎማ እንዲሁም የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ያደርጋል፡፡ የመንግስት ስልጣን በብዙ መልኩ በዜጎች ሕይወት ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡

ባለስልጣናት በህግ መሰረት እንዲሰሩ ከተገደዱ ሥልጣን የህግ ልጓም ይኖረዋል፡፡ የህግ የበላይነት የባለስልጣናትን የመወሰን ስልጣን በማጥበብ ያለአግባባ በስልጣን የመጠቀምን አሰራር ያስቀራል፡፡ በሌላ አባባል ባለስልጣናት እንደፈለጋቸው፣ አንዳሻቸው፣ በዘፈቀደ፣በተፅዕኖና በአድሏዊነት እንዳይሰሩ እና በስልጣናቸው ያላግባብ እንዳይገለገሉ ይከላከላል፡፡ ይህየሕግ የበላይነትን በጣም አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም “በዘፈቀደ ስልጣንን ከመጠቀም” ነፃ የሆነ ስርአት ለዜጎች ጠቃሚ ነው፡፡ነገር ግን ሌሎች ጥቅሞችም አሉት፡፡ ለምሳሌ በአንድ ሀገር ውስጥ አሰራሩ ሁሉ በጎቦ ላይ ከተመሠረተ እና የንብረት አጠባበቅም በባለስልጣኖች ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ ከሆነ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ሀገሪቷ አይሳቡም፡፡

የአንድ ሀገር ካፒታል የመሳብ ፍላጎት የበለጠ ሊሳካ የሚችለው የገበያ ሥርዓቱ በግልፅና በተረጋጋ ህግ ሥር የሚካሄድ ከሆነ፣ የህግ ጥበቃ ካለ፣ ውሳኔዎች አስተማማኝነት (ተፈፃሚነት) ካላቸው እና ባለስልጣናቱ በህግ መሠረት የሚሰሩ ከሆነ ነው፡፡ የመንግስት ሥልጣን ለህግ ተገዢ ሲሆን ለንግድ መስፋፋት እና ለሠራተኞች መብት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

## 2.3.2 የህግ እርግጠኝነት (ግልፅነት) እና ነፃነት

አንዱ የህግ የበላይነት መገለጫ እርግጠኝነት ነው፡፡ እርስ በእርስ ለመተማመን ቅድመ ሁኔታው የህግ የበላይነት ነው፡፡

መንግስት ሕግን ተመርኩዞ የሚሰራ ከሆነ ዜጎች እንዴት፣መቼና፣በምን ሁኔታ መንግሰት ስልጣኑን እንደሚጠቀም መገመት ይችላሉ፡፡ ዜጎች እያንዳንዱን የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን ያለ መንግስት የኃይል ጣልቃ ገብነት፣ ቅጣትና እስራት መስራት የሚችሉ መሆኑን በአስተማማኝ ሁኔታ ተረድተው በሠላም ማካሄድ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ መንግስት ሊያቀርባቸውየሚገቡ ጥቅሞችን በህግ ለማግኘትም ይችላሉ፡፡

የህግ የበላይነት ከተከበረ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሰው አብዛኛውን ወይም ሁል ጊዜ ህግን ያከብራል ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ሰው ችግር ካጋጠመው የትኛው ህግ ተፈፃሚ እንደሚሆን ያውቃል፡፡ ነፃና የማያዳሉ ፍ/ቤቶችናየህግ ተቋማት ካሉ እርግጠኝነት ይሰፍናል፡፡

ይህ ነገር በተለይ አንድ ሰው በደንብ ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት ሲፈጥር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እርግጠኝነት መኖር ሰዎችን እርስ በእርሳቸው የረጅምምይሁን የአጭር ጊዜ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያበረታታል፡፡

በተለይ ይህ ለኢኮኖሚ ሥርዓት (ግብይት) ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የህግ የበላይነት የኢኮኖሚ እድገትን ያበረታታል፡፡

ከህብረተሰባዊ ጥቅም ባሻገር እርግጠኝነት ለግል ስብዕና አስፈላጊ ነው፡፡

ሰዎች ምን አድረገው ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚያገኙ በእርግጠኝነት ካላወቁ ምርጫዎችን በመውሰድ በትክክለኛው መንገድ ሕይወታቸውን ማቀድና መምራት ይችላሉ፡፡ ይህ በማቀድ የራስን ህይወት የመመምራት ችሎታ የነፃነት አንዱ ገፅታ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ነፃነት በአንዳንድ ምክንያቶች ዕውን ላይሆን ይችላል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ድህነት ነው፡፡ ድህነት የተለየ ጉዳይ ሲሆን ነገር ግን የህግ የበላይነት አስፈላጊነትን አይቀንስም፡፡ ለነገሩ አብዛኛውን ጊዜ ድህንነት የሚመጣው የህግ የበላይነት ባለመስፈኑ የተነሳ ነው፡፡

### 2.3.3 በእኩልነት መታየት

ሶስተኛው ህግ የበላይነትንየሚያንፀባርቀው እሴት በህግ ፊት በእኩልነት መታየት ነው፡፡ ባለስልጣናትና ዳኞች በትክክል ህግን ስራ ላይ ካዋሉ ሰዎችን በህግ ፊት በማበላለጥ አያዩም፡፡ አንድን ግለሰብ ወይም ቡድንን በሙስና፣በአድልዎ ወይም ትክክለኛ ባልሆነ አመለካከት በልዩ ሁኔታ አያዩም፡፡የህግ የበላይነት አንድም ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ ሁኔታ መታየት አለባቸው በሚለው የፍትሀዊነት አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ሰዎች በእኩልነት መታየት አለባቸው ሲባል እነማን በህግ ፊት በእኩል መታየት እንዳለባቸው አያሳይም፡፡ 20ኛው ምዕተ ዓመተ ብዙአድሏዊ አሠራሮችየተወገዱበትዘመንነው፡፡ ሴቶች፣ አነስተኛ ማህበረሰቦች፣አካለ ስንኩላን እና ልጆች ብዙ መብቶችን በመጎናፀፍ በህግ ፊት በዕኩልነት ታይተዋል፡፡

ደረጃ በደረጃ ልዩነትን ከሚያስወግዱት አለም አቀፍ ድንጋጌዎች (ውሎች) ዉስጥ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትማናቸውም ዓይነት የዘር መድልዎን የሚያስወግደው ስምምነት፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማናቸውም ዓይነት ልዩነትንየሚከለከለው ስምምነት፣ ስለ ህፃናት መብቶች የተደነገገው ስምምነት፣ ከውጪ ሀገር የሚመጡ ሰራተኞችናቤተሰቦቻቸው ስላላቸው መብት የሚደነግገው ስምምነት እና ስለ አካል ጉዳተኞች መብት የሚደነግገውስምምነት አሉበት፡፡

ስለዚህ የህግ የበላይነት የሚያካትተው ሰዎችን በዕኩልነት የማየት ጉዳይ የስነሥርዓትና መስተንግዶ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው በህግ አድልዎ እንዳይደረግበት ዋስትና የሚሰጥም ጭምር ነው፡፡

ይህም ችግሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሴቶችን አቅም በመገንባትናበህግ የበላይነት አሰራር መሃከል ያለው ነገር ተፃራሪ ቢመስልም ሊጋነን አይገባም፡፡

## 3. በዓለምአቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነት አሰፋፈን

### 3.1. የህግ የበላይነት ትርጉም በአለምአቀፍ ግንኙነቶች ውስጥ

የህግ የበላይነት በብሔራዊ ደረጃ ዳብሯል፡፡ በአለምአቀፍ ህግ ውስጥ ግን ይህ ፅንስሀሳብ በስፋት አልተለመደም፡፡ ባለፉት አስርተ አመታት ግን አለምአቀፍ የህግ ስርዓትም የህግየበላይነትን ማክበር እንዳለበት እየታመነ መጥቷል፡፡

የህግ የበላይነት በብሔራዊም ሆነ በአለምአቀፍ ደረጃ ትርጉሙ ከሞላ ጎደል አንድ ነው፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች የህግ የበላይነት ሲባል ህግ መከበር እንዳለበት የሚያስገነዝብ ፅንሰሀሳብ ነው፡፡ በአለምአቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነት ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም በዋናነት የሚመለከታቸው መንግስታትንና አለም አቀፍ ድርጅቶችን ነው፡፡ ይህ ግን የህግ የበላይነትን በዓለምአቀፍ ደረጃ ተፈፃሚ እንዳይሆን አያውከውም፡፡ በአለምአቀፍ ደረጃ የዓለምአቀፍ ሕግ በሚመለከታቸው አካላት ማለትም በመንግስታትና በዓለምአቀፍ ድርጅቶች ላይ አልፎ አልፎም በግለሰቦችና በግል ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በብሄራዊ ደረጃ ባሉ የህግና የፖለቲካ ስርዓቶችና በዓለምአቀፍ ህብረተሰብ መካከል ልዩነት እንዳለ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የህግ የበላይነት ሥርዓት የሚመለከተው በመንግስትና በዜጎች መካከል ያለውን መዋቅር ነው፡፡ የህግ የበላይነት መንግስት እንዴት ተደራጅቶ ስራውን መስራት እንዳለበት የሚያሳይ ፅንሰሀሳብ ነው፡፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ ግን እንደ ብሔራዊው ዓይነት አወቃቀር (ስርዓት) የለም፡፡ዓለምአቀፍ ህብረተሰብ ከ190 በላይ ሀገሮችንና ሕብረብሔር (ዓለምአቀፍ) ድርጅቶችን ያካትታል፡፡ እነዚህን በበላይነት የሚመራ (የሚገዙለት) የዓለም መንግስታት የለም፡፡

ለምሳሌ ህግ አወጣጥን እንመልከት፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ህግ በመንግስት ይወጣል፡፡በዓለምአቀፍ ደረጃ ግን ማዕከላዊ የሆነ ህግ አውጪ አካል የለም፡፡ ህግ የሚወጣው በሀገሮችና በዓለምአቀፍ ድርጅቶች የጋራ ጥረት ነው፡፡

ዓለምአቀፍ ህግ ሁለት ዋና ዋና ምንጮች አሉት፡፡ እነሱም የልማድ ህግ እና ውል (የስምምነት) ህግ ናቸው፡
፡

የልማድ ህጎች በመንግስታት እንደ ህግ ድንጋጌ የሚቆጠሩ የመንግስታት የተለመዱ አሰራሮች ናቸው፡፡

እነዚህን ህጎች ለመተግበር ሀገራት እንደ ህግጋት ሊቀበሏቸው ይገባል፡፡ አንድን ደንብ ሀገራት የሚቃወሙት ከሆነ ደንቡ በልምድ ህግ ውስጥ መታቀፉ ይቀራል፡፡

የውል (ቃልኪዳን) ህግ ስምምነት ወይም ቃል ሊከበር ይገባል በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ስምምነቶች በሁለት ወይም ከዛ በላይ ባሉ ሀገሮች መካከል በተለያዩ ጉዳዮች የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ መንግስታት ባልተዋዋሉበት ውል ወይም ተቃውሟቸውን ባስመዘገቡበት የውል ስምምነት ድንጋጌ ሊገደዱ አይችሉም፡፡

አንዳንድ ጊዜ የውል የስምምነት ሕጎች የልምድ አለምአቀፍ ሕጎችን በአንድ ላይ አጠቃልለው ሊይዙ እና ሊያውጁ ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በብዙ ሀገራት የፀደቁ ስምምነቶች እንደ ልምድ አለምአቀፍ ሕጎች ተቆጥረው ውሎቹን ያልፈረሙ ሀገሮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ አለ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የዲፕሎማሲና የቆንስላ የቪየና ስምምነቶች፣ እ.ኤ.አ በ1949 የወጡት የጦር ቃልኪዳን (የጄኔቫ ውሎች) እና አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡

አንዳንድ ስምምነቶች በተለይም በሰብዓዊ መብቶች ላይ የተደረጉ ውሎች ለተለያዩ አተረጓገሞች የተጋለጡ ናቸው፡፡ እንደ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት፣ የመላው አሜሪካ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት፣ በየተባበሩት መንግስታት በሴቶች ላይ የሚደረግ መድልዎ አስወገጅ ኮሚቴ የመሳሰሉ ተቆጣጣሪ አካላትና ዓለምአቀፍ ፍ/ቤቶች በውሎቹ አተረጓጎም ላይ ጥሩ የሆኑ ግልፅ መመሪያዎችን (አስተያየቶችን) አውጥተዋል፡፡ ነገርግን አነዚህ ሰፊ ትርጉም ያላቸው ድንጋጌዎች ከቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ከዓለምአቀፍ ፀጥታ እና ከሞራል አኳያ የአተረጓጎም ችግሮች እያስከተሉ አንደሚቀጥሉ ግልፅ ነው፡፡

የሕግን ተፈፃሚነት በተመለከተ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ሕግን ማስፈጸም እና ሲጣስም መክሰስና መቅጣት የመንግስት ኃላፊነቶች ናቸው፡፡በዓለም አቀፍ ደረጃ ግን ፖሊስ፣የተማከለየገደብ (የቅጣት) ስርዓት ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የከሳሽ መ/ቤት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕግ የሚከበረው በብዛኛው በራስ ተነሳሽነት ነው፡፡ ሀገሮች በራሳቸው ሕግን

ያስፈጽማሉ ወይንም ደግሞ ትብብርን ይጠይቃሉ ፡፡ በ3.2.3 ክፍል በዚህ ረገድ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክር ቤት ሚና ተብራርቷል፡፡

ሆኖም እነዚህ በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የሕግ አሠራር ልዩነቶች የሕግ የበላይነት ትርጉምን ሆነ መስፈርቶቹን አይቀይሩም፡፡ነገር ግን የሕግ የበላይነትንበዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስፈን ጥቂት ፈታኝ ሁኔታዎች መኖራቸው አይካድም፡፡

## 3.2.በዓለምአቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች (መስፈርቶች)

### 3.2.1. ዓለምአቀፍ ሕግ ግልፅ፣ ይፋ፣ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል (ተደራሽ) እና አመላካች መሆን አለበት

በዓለም አቀፍ ህብረተሰብ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ሕጎችም ይፋ ተደራሽ ግልፅ እና የሚተገበሩ መሆን ያለባቸው ሲሆን ሕግ አወጣጡም ግልፅ መርህ ሊኖረው ይገባል፡፡ከዚህ አንፃር በብሔራዊውና በአለም አቀፍ ህጎች መሃከል ልዩነት የለም፡፡

ላይ ላዩን ሲታይ ዓለም አቀፍ ሕግ ከብሔራዊው ሕግ ይልቅ ብዙ ፈተናዎች አሉበት፡፡ ይህም የሚሆነው በአለም አቀፍ ደረጃ ዓለም አቀፍ ሕግ ግልጽነት፣ ተደራሽነትናእርግጠኝነት እንዲኖረው ኃላፊነት የሚወስድ ማዕከላዊ ሕግ አውጪ ስለሌለ ነው፡፡ ይቁልንም ዓለም አቀፍ ሕግ እርግጠኝነት እንዲኖረው የማድረግ ኃላፊነቱ የሚወድቀው በራሳቸው በመንግስታቱ ላይ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታየት የሚገባቸው ጉዳዩች አሉ፡፡ ውሎች የድርድርና የመቻቻል ውጤቶች ስለሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ግልፅ አይደሉም፡፡ የሁለት እዮሾችና የብዙ ተዋዋይ የሆኑ ውሎች ስላሉ መንግስታት ያሏቸውን መብቶችና ግዴታዎች በሙሉ ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ እዚህ ላይ የዓለም አቀፍ ሕግ መዝገብ ቤቶች ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት፡፡ በተለይ የየተባባሩት መንግስታት ድርጅት የስምምነቶች ስብስብንመጥቀስ ይገባል፡፡

አንዳንድ በተለይ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የሚወጡ ስምምነቶች የተለያዩ ትርጉሞች ያሏቸው አንቀጾች አሏቸው፡፡ አንዳንድ የውሎችን ተፈፃሚነት የሚቆጣጠሩ ከላይ የተጠቀሱት አካላት የውሎቹን ትርጎሞች በማብራራት ግልፅ ያደጋሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ በፊት ውሳኔ ከተሰጠባቸው አቤቱታዎች ተነስተው ለተመሳሳይ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያላቸውን ፍርዶች እና የሕግ አተርጓጎሞች ይበይናሉ፡፡

የልማድ ሕግ በአጠቃላይ ግልፅ ቢሆንም በዝርዝር ከታየ ግን ግድፈቶች አሉት፡፡ ምንም እንኳን ለማስተካከል ብዙ ጥረት ቢደረግም በብሔራዊ ደረጃ ዳኞች የወሰኗቸውና በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ ተጽዕኖ ያሏቸው ፍርዶች በብዛት አይታወቁም፡፡ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ መርሖዎችን አሟልቶ የያዘ ገዢ ጥንቅር የለም፡፡

በብሔራዊ የሕግ ስርዓቶችም ከእነዚህ ችግሮች ጥቂቶቹ አሉ፡፡ ለምሳሌ የሰብዓዊ መብቶች አተረጓጎም ላይ አሻሚነት አለ፡፡በብዙ የሕግ ዓይነቶች በዝርዝር ሕጉ ምን እንደሚል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ችግሮቹ በብሔራዊም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ያን ያህል የሚጋነኑ አይደሉም፡፡

አሁን አሳሳቢው ነገር የዓለም አቀፍ ሕጎችና ተቋማት መብዛት ነው፡፡ የታወቁ ታዛቢዎች እንደሚሉት ዓለም አቀፍ ሕግ እየተፈረካከሰ እና ወደ ተለያዩ አነስተኛ ሕጎች እየተበተነ ነው፡፡ አንዳንዶች እንደሚፈሩት

ድንጋጌዎቹ ወደፊት እርስበርስ የሚጋጩ እንደሚሆኑ፣ ግጭቶቹን ለማስማማትምእንደሚያስቸግር እና የአለም አቀፍ ሕግ ግልፅነት፣ይፋነት እና እርግጠኝነት እንደሚጠፉ ነው፡፡

አሁን ግን በቅርቡ የወጣ የየተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን ሪፖርት እንደሚያሳየው እነዚህን ግጭቶች የሚፈቱ ዘዴዎች እንዲዳብሩ ከተሰራ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ይፈታሉ፡፡

በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ሕግ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡ የ1969 የቪየና የዓለም አቀፍ ውሎች ቃልኪዳን ስለ ስምምነቶች (ውሎች) መፈራረም እና ማቋረጥ ያስቀመጣቸው ሕጎች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ለሕግ የበላይነት ሥርዓት መስፈን አንደ አንዱ መሰፈርት የሚቆጠረውን ግልጽነትንቢያንስ ውሎች (ዓለም አቀፍ ስምምነቶች)ማሟላት እንደሚገባቸው ይህ ቃልኪዳን ስለሚደነግግ አድናቆት ሊቸረው ይገባል፡፡

በተጨማሪም ኢንተርኔት ዓለም አቀፍ ስምምነትን (የውል ሕግን) የበለጠ ለሕዝብ ክፍት (ይፋ) አድርጎታል፡፡ የየተባበሩት መንግሥታት የውል ስብስብን በድረገጽ ማግኘት ይቻላል፡፡ የአንዳንድ ፍ/ቤቶች ፍርዶች ከነትችቶቻቸው ታትመው ይገኛሉ፡፡ ለአብነት የዓለም አቀፍ ፍ/ቤት እና የዓለም አቀፍ የወንጀል ችሎቶች የፍርድ መድብሎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የዓለም አቀፍ ሕግ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እነኚህ ብቻ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡ ከዚህ በበለጠ መተንተን ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን ያልተማከለ ቢሆንም ዓለም አቀፍ ሕግ በበቂ ሁኔታ ግልጽ፣ እርግጠኛ እና ሊገመት የሚችል ነው፡፡ ይህ አባባል የዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት፣ የጦርነት ጊዜ ሰብዓዊነት ሕግ፣ የሠራተኛ፣ የኢኮኖሚ፣ የባሕር እና የሐገራት ኃላፊነትን የሚመለከቱ ዋና ዋናዎቹን ዓለምአቀፍ ሕጎችን በሚመለከት እሙን ነው፡፡

ይህ ግን ሁሉም ነገር የሚያስመካ ነው ማለት አይደለም፡፡ ዓለምአቀፍ ሕግ በግልጽነቱ፣ በእርግጠኝነቱና በተደራሽነቱ ዙሪያ ሊሻሻል የሚገባውና የሚችል ነው፡፡

### 3.2.2 ገለልተኛና ነጻ ፍርድ ቤት

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን በጣም ፈታኝ የሆነው ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ነው፡፡ ሁለት አይነት ሰላማዊ የግጭት አፈታት መንገዶች ሲኖሩ እነርሱም ዲፕሎማሲ እና በፍርድ መዳኘት ናቸው፡፡ ብዙ ግጭቶች በዲፕሎማሲ ማለትም በድርድር፣ በእርቅ፣ እውነታን በማጣራትና በማቀራረብ ይፈታሉ፡፡ ይህ ካልተሳካ ግን ባላንጣዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍ/ቤት አምጥተው ጉዳዩ ውስጥ በሌለበት በ3ኛ ሰው ይዳኛሉ፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዳኝነት ሰጪ አካላት እጥረት የለም፤ እንዲያውም አንዳንዴ የሚተቸው መብዛታቸው ነው፡፡

በፍርድ የመዳኘት ጉዳይ በግልግል ዳኞች (ለምሣሌ በቋሚ የግልግል ፍ/ቤት ወይም ለአንዲት ጉዳይ በተሰየሙ ገላጋይ ዳኞች) ወይም በፍ/ቤት ፊት ሊካሄድ ይችላል፡፡

በዓለም ውስጥ ወደ 15 የሚጠጉ ዓለም አቀፍ እና አካባቢያዊ ፍርድ ቤቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የዓለም አቀፍ ፍ/ቤት (በየተባሩት መንግሥታት ስር)፣ ዓለም አቀፍ የባህር ችሎት፣ ዓለም አቀፍ የወንጀል ችሎት፣ የአውሮፓ ፍ/ቤት፣ የአውሮፓ የሰብአዊ መብት ፍ/ቤት፣ የደቡብና የሰሜን አሜሪካ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዓለም አቀፍ የተዋቀሩ የፍርድ አካላት የገለልተኝነትና የነጻነት ጉዳይም መታየት አለበት፡፡ የዓለም አቀፉ ፍ/ቤትም ሆነ የሌሎቹ ችሎቶች ዳኞች በከፍተኛ ችሎታቸውና ሥነምግባራቸው ይታወቃሉ፡፡ የዓለም አቀፍ ፍ/ቤት የየተባበሩት መንግስታት አባል ለሆኑም ሆነ ላልሆኑ ሀገራት ክፍት ነው፡፡

የእነዚህ የዓለም አቀፍ የፍትሕ አካላት ትልቁ ፈተና የዳኝነት ሥልጣናቸው ነው፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች አንድን ፍ/ቤት እኛን ለመዳኘት ሥልጣን የለውም ወይም አለው ብለው መወሰን አይችሉም፡፡ ይህ ከሆነ የህግ በላይነት አይሰፍንም፤ ግጭታቸውም አይፈታም፡፡

በእርግጥም በብሔራዊ ደረጃ የሕግ የበላይነት ፍ/ቤቶች አስገዳጅ ሥልጣን እንዲኖራቸው ይፈልጋል፡፡ ይህም በሁለት ተከራካሪ ወገኖች መስማማት ወይም አለመስማማት ላይ ተመሥርተው ሳይሆን ብቃቱ ኖራቸውም አልኖራቸው በገለልተኝነት ፍርድ ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡

ሆኖም አንዳንድ ከላይ የተጠቀሱ የዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ ሥልጣን አላቸው፡፡ ለምሣሌ የአውሮፓ ሀገሮች በአውሮፓ የሰብአዊ መብት ፍ/ቤት ለመዳኘት ካልተስማሙ የአውሮፓ ሀገሮች ም/ቤት አባል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ባንጻሩ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች ከተከራካሪ ወገኖች ፈቃደኝነት ውጪ የመዳኘት ሥልጣን የላቸውም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ዓለም አቀፍ ፍ/ቤት ነው፡፡

በዚህም ምክንያት ተከሣሽ ሀገሮች ከፈለጉ ከከሣሽ ሀገሮች ጋር ያላቸው አለመግባባት በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት እንዳይፈታ ሊከላከሉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ግጭቶቹ ሳይፈቱ ይቆያሉ፡፡

ይህ መጥፎ ገጽታዎች አሉት፡፡ ዓለም አቀፍ ሕግን በቅጡ እና በግልጽ እንዳይታወቅ ያደርገዋል፡፡ ሕጉም ባለመታወቁ የተነሣ ግጭቶች በዲፕሎማሲ የመፈታት እድላቸው ይቀጭጫል፡፡

በፍ/ቤቱ ማቋቋሚያ አንቀጽ 36(2) መሠረት ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ እንዲዳኛቸው ከፈቀዱ ሀገሮች ጋር የሚከራከሩ ሀገሮች ካሉ እነሱም ለዚያች ጉዳይ ለመዳኘት በመስማማት ብቻ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የሚያገኝበት ሁኔታ አለ፡፡ አሁን ይህ አንቀጽ ብዙም አይሠራበትም፡፡ እስካሁን ድረስ 67 ሀገሮች ብቻ ሁሌ ለመዳኘት

ፈቅደዋል፡፡ ከእነርሱም አብዛኛዎቹ ሌላይኛው ተከራካሪም ወገን በማናቸውም ጊዜ ለመዳኘት ይስማማ የሚል ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አንቀጹን ውጤት አልባ አድርገውታል፡፡

በእርግጥ በዓለም ላይ የህግ በላይነት እንዲሰፍን ከተፈለገ በአንቀጽ 36(2) የተቀመጠውን የዓለም አቀፉን ፍ/ቤት አስገዳጅ የዳኝነት ሥልጣን ሀገሮች እንዲቀበሉት ያስፈልጋል፡፡ አውሮፓ ለዚህ ጥሩ ምሣሌ ነው፡፡ የአውሮፓ ሀገሮች የአውሮፓ ም/ቤት አባል እና አውሮፓ ሕብረት አባል የሚሆኑት ሉክሰንበርግ የሚገኘውን የአውሮፓ የፍትሕ ፍ/ቤትን እና ስትራስበርግ የሚገኘውን የአውሮፓ የሰብአዊ መብት ፍ/ቤትን የመዳኘት ሥልጣንን የሚቀበሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ባይሆኑም የተወሰኑ የአውሮፓ ሀገሮች የዓለም አቀፍ ፍ/ቤትን ዳኝነት አልተቀበሉም፡፡ ፍ/ቤቶች፣ ዳኝነት ሰጪ ተቋማት እና ሕጎች በበዙ ቁጥር ሊከሰት የሚችለው ሌላው ችግር የዳኞች ዓለምአቀፍ ሕግን ሁልጊዜ በወጥነት የመተርጎም ከባድነት ነው፡፡ ግን ይህን የሚፈቱት በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሌሎች ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች በመመልከትና እርስ በእርስ በመመካከር ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶችን በመፍጠር ነው፡፡ ይህ አይነቱ ግንኙነት ዓለምአቀፍ ሕግን ለመተርጎምና ግልጽነትን ለማስፈን ይረዳል፡፡

### 3.2.3 በቂ የሆነ የፍርድ (የሕግ) አፈጻጸም

ሉዊስ ሄኒኬን የሚባል አንድ የዓለም አቀፍ ሕግ ጠበቃ በአንድ ወቅት ሁሉም ሀገሮች ሁሉንም የዓለምአቀፍ ሕግ መርሆዎችና ግዴታቸውን በሙሉ ሁል ጊዜ ማክበራቸው አይቀሬ ነው ሲል ጽፎ ነበር፡፡

ምንም እንኳን ዓለም አቀፍ ሕጎች አንዳንዴ የሚጣሱበት፣ የሚዘገቡበትና የሚያወያዩበት ሁኔታ ቢኖርም ይህ ሁሌ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚያጋጥም ነው፡፡ ብዙዎች ዓለምአቀፍ ሕግ ይከበራል ብለው ይቀበላሉ፡፡ ስለዚህ ሕጉን ማስፈጸም ብዙ ችግር አይመስልም፡፡

ሁኔታው ግን አጥጋቢ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ሕጉን የሚያስከብር ብቸኛ ጡንቻ ያለው ማዕከል በዓለም አቀፍ ደረጃ የለም፡፡ በእርግጥ ይህንን ማድረግ የሚችሉ አንዳንድ አካላት አሉ፡፡ ሆኖም ከእነዚህ አካላት አብዛኛዎቹ ውጤታማ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

ከእነዚህ አካላት ውስጥ ዋናው የተ.መ.ድ. የጸጥታው ምክር ቤት ነው፡፡ ይህ አካል የዓለም ጸጥታና ሠላም አደጋ ውስጥ ከወደቀ ኃይል እስከመጠቀም ድረስ የሚያደርሱ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡ የየተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ም/ቤት ለየትኛውም ወገን አያዳላም ለማለት ያስቸግራል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የምክር ቤቱ ቋሚ አባላት አንዳንዴ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብትን በመጠቀም ዓለምአቀፍ ሕግ ሲጣስ እርምጃ እንዳይወሰድ ስለሚያደርጉ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም እራሳቸው የምክር ቤቱ ቋሚና ቋሚ ያልሆኑ አባላት የየተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተርን ሲጥሱ ይታያል፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን እንደ የተባባሩት መንግስታት የፃጥታው ም/ቤት ያሉት አካላት በተለይም እንደ ሰላምና ፀጥታ ያሉ የዓለም አቀፍ ማህረሰብ ጥቅሞችን የሚመለከቱ የዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰቶችን

ቢመለከቱም ከዛ በመለስ (በየተባበሩት መንግስት ቻርተር ‹መተዳደሪያ ደንብ› ወስጥ የማይወድቁ) ሌሎች አለመግባባቶችን የሚዳኝ አካል ብዙም የለም፡፡ እንዲሁም ይህ ዓለም አቀፍ ፍ/ቤትም ቢሆን የዳኝነት ስልጣኑ በተሟጋቾች መንግስታት ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አለመግባባቶች በፍ/ቤት የሚፈቱበት ዕድል የጠበበ ነው፡፡

ስለዚህ በመንግስታት የግል ግንኙነቶች ውስጥ ሕግ ተጦሶ ቢገኝ ተጎጂው መንግስት ያለው ብቸኛ መፍትሄ የራስ አገዝ እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ መንግስታት በእንግሊዝኛው “ሪቶርዥን” “ብቀላ” ተብለው የሚጠሩ የኢኮኖሚ ማዕቀብ፣ ወደ ሀገር የመግባት (የጉዞ) ክልከላ፣ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ማቋረጥ የመሳሰሉ ህጋዊ የበቀል እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ ፡፡ እንዲሁም መንግስታት በባህሪያቸው ህገወጥ የሆኑ ነገር ግን ቀደም ሲል ከተፈፀመባቸው ህገወጥ ጥቃት አንፃር አግባብነት ያላቸው በጦር ከተማን እንደመከበብ የመሳሰሉ እርምጃዎችን መወሰድ ይችላሉ፡፡

የራስ አገዝ እርምጃ ችግሩ ውጤታማነቱ እንደሀገሮቹ ጥንካሬ የሚወሰን መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም መጀመሪያነገር ሕግ ስለመጣስ የሚዳኝ ገለልተኛ 3ኛ ወገን ዳኝነት ባልሰጠበት ሁኔታ መብቴ ተጥሷል በማለት ብቻ የሚወሰድ እርምጃ መሆኑ ሌላው ችግር ነው፡፡ እርምጃመወሰድ ያለበት ሕግ ስለተጣሰ እንጂ አቅም ስላላ ብቻ መሆን የለበትም፡፡

## 3.3. የሕግ የበላይት ለምን በዓለምአቀፍ ደረጃ የግድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የሕግ የበላይነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው ጥቅም በብሔራዊ ደረጃ ካለው ጥቅም ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ይነገራል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነት የዓለም አቀፍ ሕግ በሀገሮች ወይም በሚመለከታቸው አካላት (ሰዎች) መካከል በእኩልነት እንዲሰፍን፣ተገማች እንዲሆን እና ስልጣንና ዐቅምን ያለግባብ መጠቀም እንዳይፈጠር ይረዳል፡፡ ሆኖም መንግስታትም ሆኑ አለምአቀፍ ደርጅቶች ወይም ግለሰቦች ዓለም አቀፍ ሕግ እንዲያከብሩ የሚፈለግበት ሌሎች ምክንያቶች አሉ;፡፡

መጀመሪያ ነገር አለም አቀፍ ሕግ በመንግስታት መካከል ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ተብሎ የወጡ ህግጋትና እና አሰራሮች ስብሰብ ነው፡፡ ለአብነት የጦር ሕግን ብንወስድ በጦርነት ውስጥ ሰብዓዊነትን ለማስፈን ታስቦ የወጣ ነው፡፡

የዓለም አቀፍ ሕግ ባይኖር ወይም ባይከበር ኖሮ ሰላምና ደህንነትን ማስፈን አስቸጋሪ በሆነ ነበር፡፡ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚመራበት የዓለም አቀፍ ሕግጋት ባይኖሩት ኖሮ የበለጠ ግጭትና ቀውስ ይፈጠር ነበር፡ ፡ እንዲሁም የጦር ሰብዓዊነት ሕግ ባይኖር ኖሮ ጦርነት ይበልጥኑ አሰቃቂ በሆነ ነበር፡፡

ከዚህ በበለጠ ዓለም አቀፍ ሕግ ዓለምአቀፋዊም ሆነ አካባቢያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በይበልጥ እየጣረ ይገኛል፡፡ በምሣሌነት ዓለምአቀፍ ወንጀልን፣ ዓለምአቀፍ ሽብርተኝነትን፣ የገንዘብ ግብይት መቃወስን፣ የአካባቢ ስጋትን (የአየርና የባህር ብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመር፣ ዝርያቸው ከምድረገጽ እንዳይጠፉ

የሚያስጉ የዱር አራዊት፣ የኒውክሊየር እና የአደገኛ ምርቶች አደጋ) ማንሳት ይቻላል፡፡ እነኚህ ጉዳዮች አገሮች ብቻቸውን የሚፈቷቸው ችግሮች ሳይሆኑ ዓለም አቀፍ ትብብሮችን እና ደንቦችን ይሻሉ፡፡ በዓለምአቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነት መስፈን የአካባቢያዊ (አህጉራዊ) እና ዓለምአቀፋዊ ችግሮች መፍትሔዎችን ያቀራርባል፡፡

ዓለም አቀፍ ሕግ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች በመላው ዓለም ላይ ትኩረት እየሰጠ መጥቷል፡፡ እንደ ዓለም አቀፉ ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች በብሄራዊ ሕገ መንግስቶች ተቀምጠዋል፡፡ ይህም ሆኖ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ህጎች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጎች አማካኝነት የተረጋጋጡ እና የፀኑ ናቸው፡፡

እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሕግ፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤቶች እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቆጣጣሪ

አካላት በብሔራዊ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ላይ ቁጥጥር ያደረጋሉ፡፡ በሀገር ውስጥ ያለውን የቁጥጥር ሥርዓት ያግዙታል፡፡ ለዓለም አቀፍ ሕግ መገዛት በብሔራዊ ደረጃ ላይ ያሉ ያሰብዓዊ መብት ጥበቃዎች እንዲጠናከሩ ያበረታታል፡፡ ስለዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕግ የበላይነት መኖር የዜጎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ይጠቅማል፡፡

## 4. በብሔራዊና በዓለምአቀፍ ደረጃዎች ያሉ የሕግ የበላይነት ስርዓቶች መካከል ያለው ትሰሰር

### 4.1. በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት

የሕግ የበላይነት በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ተመሳሳይ ባሕርያት አሉት፡፡ትርጉሙበሁለቱም መስኮች አንድ ነው፡፡ የህግ ይፋነት፣ግልጽነት፣ ተደራሽነት፣ በእኩልነት ስራ ላይ መዋል እና ነፃና ገለልተኛ ፍ/ቤትመኖር አለበት፡፡

ለመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የሕግ የበላይነት በሀገር ውስጥ ካለው የሕግ የበላይነት ስርዓት ጋር ይዛመዳል? በዓለም አቀፍ ያለው ሀገር ውስጥ ካለው የሚያገኘው ጥቅም አለ? በሀገር ውስጥ ያለው የሕግ

የበላይነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለው የሕግ የበላይነት አማካኝነት ይጠናከራል?

ቀደም ባለው ጊዜ በሁለቱ ስርዓቶቹ መካከል ያለው ግንኑነት አይጠቀስም ነበር፡፡ ባሁኑ ወቅት ግን ሁለቱን ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡ ቢያንስ በሁሉም የህግ ዘርፎች አንኳን ባይሆን የግንኙነታቸው መጠን እየተጠናከረ መጥቷል፡፡

ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ሕገ መንግስት ነው፡፡ በተለያዩ ሀገሮች ሕገ መንግስቶች ውስጥ የተጠቀሱት የሰብዓዊ መብቶች ሕጎች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብትሕጎች ውስጥ ከተጠቀሱት ሕጎች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ አንድ አዲስ ሕገ መንግስት ሲወጣ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሰነዶችን ማጠቀስ በአሁኑ ጊዜ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በአንዳንድ ሕገ መንግስቶች ዓለም አቀፍ ሕግ የብሔራዊው ህግ አካል እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡

በሌሎችምእንደአካባቢ እና ኢንቨስትመንት በመሳሰሉ ሕጎች ዙሪያ የአለም አቀፍና ሃገራዊ ህጎች ትስስር ይታያል፡፡ የፓርላማ አባል የሆኑ የፓለቲካ ሰዎች በአለም ላይ ስምምነቶች (ውሎች) እየበዙ በሄዱ ቁጥር

የሀገራት ፓርላማዎች ስልጣንና ተግባር እየቀነሰ እንደሚሄድ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ሕግአውጭዎች በብሄራዊ ደረጃ ህግ ሲያወጡ የሚወጡት ሕጎች ከአለም አቀፍ ውሎች ጋር እንደሚሄዱ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ለዚህም "ፓርላማና ዲሞክራሲ በ21ኛው ምዕተአመት" ሚለውን ህትመት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መመሪያ በስተመጨረሻ ላይ ተጠቅሷል፡፡

በተለይ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ አንድ ሕግ ከሀገሪቱ ሕገ መንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግጋት ጋር በሚሰማማ መልኩ የማይጋጭ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ፓርላማዎች ዓለም አቀፍ የሰብኣዊ መብት ሕጎች በስራ ላይ እየዋሉ እንደሆነ ማየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ከላይ የተጠቀሰውህትመት ለአብነት በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ እንዴት እንደሚሰራ አስቀምጦታል፡፡ የብራዚል ፓርላማ የአሜሪካ አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነት ተቆጣጣሪ አካልን አስተያየቶች ሥራ ላይ የዋለበት መንገድ በዚህ ረገድ አስደናቂ ነው፡፡ ለፓርላማ አባላት ሰብዓዊ መብትን አስመልክቶ በአቡጃ በእ.ኤ.አ. 2004 ዓ.ም በተደረገ ጉባኤና እንዲሁም የፓርስ መርሆች ተብለው በሚታወቁት (በተ.መ.ድ መግለጫ 48/134 እ.ኤ.አ. 1993 የወጡት) ግንዛቤዎችንና መመሪዎችንመመልከት ይቻላል፡፡

ይህ ማለት ግን ሁሉም የዓለም አቀፍ ሕግ ድንጋጌዎች በብሔራዊ ሕግ ውስጥ ተካተዋል ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም በተቃራኒው በብሄራዊ ህግ ውስጥ ያሉትም በዓለም አቀፍ ሕግ ውስጥ አሉ ማለትም አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድ ሀገር ራሱን ለመከካል ሲል በሌላ ሀገር ውስጥ ጣልቃ ከገባ ጉዳዩ የብሔራዊ ሕግ ሳይሆን የዓለም አቀፍ ሕግና የተ.መ.ድ. ቻርተር ጉዳይ ይሆናል፡፡

ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት ዓለም አቀፍ ፍ/ቤት እንጂ የሀገር ውስጥ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ እዚህ ላይ የአለም አቀፍ ፍ/ቤት በተጨባጭ ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ሌላ ነገር ነው፡፡

በተመሳሳይ በአንድ የመሬት ባለቤት ግለሰብ እና በሚኖርበት ከተማ ማዘጋጀ ቤት መካከል በግንባታ ፈቃድ ጉዳይ ክርክር ቢነሳ ተፈጻሚ የሚሆነው የብሔራዊ ሕግ ከመሆኑም በላይ ዳኝነት የሚሰጠውም ዓለም አቀፍ ሳይሆን ብሔራዊ ፍ/ቤት ነው፡፡

ሆኖም በጉዳዩ ላይ በሥራ ላይ የሚለው ሕግ ከዓለምአቀፍ ሕግ ጋር መጣጣም ያለበት መሆኑ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ የአውሮፓ ሃገር ያለ የመጨረሻው ደረጃ ፍ/ቤት የአውሮፓን ሰብዓዊ መብቶች ስምምነት የሚጥስ ውሳኔ ከበየነ ጉዳዩ ለአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ የአሮፓ ሰብአዊ መብቶች ፍ/ቤት ስምምነቱ የተጣሰ መሆኑን ካመነ ይህ ሀገር ህጉን እንዲያሻሽልና ዳግመኛ ጥሰት እንዳይፈፀም ያደረጋል፡፡

ለምሳሌ ባንድ ወቅት የአውሮፓ ሰብዓዊ መብቶች ፍ/ቤት የአውሮፓ ስብዓዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 6 መጣሱን ወስኗል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አንድ መንግሥታዊ አካል በአንድ ዜጋ መብቶች ላይ ውሳኔ ከሰጠ ዜጋው አቤቱታ የሚያቀርብበትና ፍ/ቤት የሚሄድበት መንገድ ስላልነበር ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ

በቁጥጥር ስር ውሎ በኋላ የተለቀቀን ወይንም ክሱ የተሰረዘለትን ዜጋ የዲኤንኤ(DNA) ናሙናዎች ይዞ ማቆየት የአውሮፓ ሰብዓዊ መብቶች ፍ/ቤት የአንድን ሰው የግል ነጻነት መብትን የሚጻረር መሆኑን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በእነዚህም ሁለት ጉዳዮች ሀገሮቹ ሕግ የማውጣት/የማሻሻል እርምጃ ለመውሰድ ተገደዋል ፡፡

ስለዚህ በአጠቃላይ በሃገር አቀፍና በዓለም አቀፍ የሕግ የበላይነት መካከል እየተጠናከረ የመጣው ግንኙነት አንደኛው ለአንደኛው ጥንካሬን የሚሰጥ ነው፡፡

## 4.2 በአገር ውስጥ ያለው የሕግ የበላይነት ለምን በዓለምአቀፍ ሕግ ላይ

## ጥገኛ ይሆናል?

ዓለም አቀፍ ሕግ፣ በአገር ውስጥ ለሚኖረው የሕግ የበላይነት አግባብነት አለው፡፡ ለምሳሌ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግሃገሮች የዜጎቻቸውን በነፃት የመናገር፤ የመሰብሰብ፣ የማምለክ መብቶችን እንዲያከብሩ ይደነግጋል፡፡ ሀገሮች በዜጎቻቸው ላይ ያላቸውን ሥልጣን ይገድባል፡፡ ምሣሌ ዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 6-12፡፡ የዚህ ስምምነት አንቀጽ 14 ደግሞ ነጻና ገለልተኛ የሆነ ፍ/ቤት እንዲኖር ያዛል፡፡

### ሰብዓዊ መብቶች

ከሞላ ጎደል ሁሉም ሃገሮች የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ፈርመዋል፡፡ ለምሳሌ እስከ ነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) ድረስ አቀፍ የኢኮኖሚ፤የሶሻልና የባህል መብቶች ስምምነትን የፈረሙ ሃገሮች 160 የነበሩ ሲሆን፣ ዓለምን አቀፍ የሲቪል እና የፖሊቲካ መብቶች ስምምነትን የፈረሙት ደግሞ 167 ነበሩ፡፡ በተጨማሪም አካባቢያዊ (አህጉራዊ) የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች አሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ባለሥልጣን ሃገሩ የትኞቹን ውሎች እንደፈረመች ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

በተጨማሪ ብዙ ሰብዓዊ መብቶች ወደ ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግነት ተቀይረዋል፡፡ሁሉአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ሆኗል፡፡ ይህ ማለት ሃገሮች ዓለም አቀፍ ውሎችን ተቀብለው ቢያጸድቁም ባያፀድቁም መሠረታዊ የሚባሉየሰብዓዊ መብቶችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ በሀገሮች ሕግ ውስጥ ወሣኝ ተፅዕኖ ሊኖረው ይገባል፡፡

### የዓለም አቀፍ ሕግ የበላይነት

ዓለም አቀፍ ሕግለብሔራዊ ሕግ የባላይ ነው፡፡ ሃገሮች የዓለም አቀፍ ሕግ ተገዢ ናቸው፡፡ ሕግ አውጭው፣ ሥራ አስፈፃሚው ሆነ ፍ/ቤቶች ዓለም አቀፍ ሕግ ከጣሱ መንግስት ተጠያቂ ነው፡፡ ሃገሮች በብሔራዊ ሕጋቸውን ወይም ሕገመንግስታቸውን የዓለም አቀፍ ሕግ ለመጣስ እንደ ሰበብ (ምክንያት)

ሊጠቀሙባቸው አይችሉም፡፡ በሌላ አነጋገርዓለም አቀፍ ሕግ በብሔራዊ ሕግ እንኳንስ ሊሻር ችላ ሊባል እንኳንአይችልም፡፡

ዓለም አቀፍ ሕግ፣በተለይ ደግሞ የሰብዓዊ መብት ሕጉ በብሔራዊ ደረጃ የሚኖርን የሕግ የበላይነት ያጠናክራል፡፡ በአንድ ሃገር የሕግ የበላይነት ሥርዓት ውስጥ ክፍተቶች ካሉ እነርሱን ለመሙላት ዓለም አቀፍ ሕግን መጠቀም ይቻላል፡፡

## አንዳንድ ገደቦች

በእርግጥ ነበራዊ ሁኔታዎች ሲታዩ ብዙ የማይጥሙ ነገሮች አሉ፡፡ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግ አስገዳጅነት በተለያዩ መንገዶች በሀገሮችውስጥ ሊገደብ ይችላል፡፡

የመጀመሪያው ችግር አንዳንድ የሥምምነቶቹንአንቀጾች ሃገሮቹ ያለመቀበላቸው ወይም ቅሬታቸውን ማስመዝገባቸው ነው፡፡ሀገሮች አንድን ውል ሲቀበሉከራሳቸው አንፃር አንዳንድ አንቀጾችን ወይም ሕጎችን እንደማይቀበሉ ይፋ ያደርጋሉ ወይምያሻሽሏቸዋል፡፡

አካራካሪ የሚኖነው የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ በየትኞቹ ላይ ገደብ (ቅሬታ) ማስቀመጥ እንደሚችሉ ነው፡፡ ብዙዎች ቅሬታ ማስቀመጥ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን ዓላማ ይፃረራል ብለው ይከራከራሉ፡፡ ሃገሮች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ላይ ቅሬታ ካስቀመጡ በሃገራቱ ውስጥ የሕግ የባለይነትን ሊጎዳ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡

## በብሔራዊ ደረጃ ያለው ተፈጻሚነት

ሁለተኛው ችግር በሃራት ውስጥ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ሕጎች መካከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡ ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ዓለም አቀፍ ሕግ በአገር ውስጥ ሕግ ላይ የበለይነት አለው፤ መንግሥታትም ሊያከብሩት ይገባል፡፡ ጥያቄው ግን ዜጋና ዜጋ ወይም ዜጋና መንግስት በብሔራዊ ፍ/ቤት ውስጥ ዓለም አቀፍ ሕግን እየጠቀሱ ሊከራከሩበት ይችላሉ ወይ የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ሶስት የሚሆኑ መልሶች አሉ፡፡

## አሀዳዊና ሁለትዮሽ ሥርዓቶች

የዓለም አቀፍ የውል ሕጎች ስምምነቶች በብሔራዊ ደረጃ በሁለት መንገዶች ይስተናገዳሉ፡፡ እነዚህም አሀዳዊና ሁለትዮሽ መንገዶች ሲሆኑ ፖሊቲከኞች ሃገራቸው የትኛውን ሥርዓት እንደምትከተል ማወቅ ይገባቸዋል፡፡

በአገራዊው ሥርዓት፤አንድ ሃገር የፈረመቻቸው የትኛውን ሥርዓት እንደሚከተል ማወቅ ይባቸዋል፡፡

በአሀዳዊው ሥርዓት አንድ ሃገር የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ የውል ስምምነቶች በቀጥታ እንደ ሀገሪቷ ሕግ ይቆጠራሉ፡፡ ለምሣሌ አንድ መንግስት በዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት ላይ የተጠቀሱትን አንቀፆች በመፃረር የአንዱን ዜጋ ሃሣብን የመግለጽ መብት ከተፃረረ ዜጋው አንቀጹን ጠቅሶ በአገሩ ፍ/ቤት መንግሥትንሊከስ ይችላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ሕግ እራሱን በራሱ ሥራ ላይ ያውላል፡፡በሃገሪቷ ሕግ ላይ ቀጥታ ተፅዕኖ አለው፡፡ያላንዳች ቅድመ ሁኔታዎች የሀገሪቱ ህግ አካል

ይሆናል፡፡ ፍርፍ ቤቶችም የዓለም አቀፍ ሕጉን የሚያፀና ሌላ ሕግ መውጣት ሳያስፈልግ በቀጥታ ሥራ ላይ ያውሉታል፡፡

በሁለትዮሽ ሥርዓት በዓለም አቀፍ ውሎች ውስጥ ያሉ ሕጎች. ወደ ብሔራዊ ሕግ ከተለወጡ (ከተሸጋገሩ)

በኋላ በሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ይህም ይህን ሥርዓት የሚከተሉ ሃሮች በመጀመሪያ ብሔራዊ ሕጋቸውን አጢነው ቀጥለው ዓለም አቀፉ ውል ከእነርሱ ሕግ ጋር መጣጣሙን አይተው እና አጣጥመው ውል ስምምነቱን ያፀድቃሉ ማለት ነው፡፡

በሁለቱም አሠራሮች የዓለም አቀፍ ውሉን በፈረሙበት አገሮች መካከል ይፈፀማል፡፡ ይህም ሕጎች ከተጣሱ የፈረሙት ሃገሮች እርስ በርስ ለምን ይህ እንደሆነ ይጠያየቃሉ ማለት ነው፡፡ ስዚህ አንድ ሃገር የአንድን ዜጋ የመናገር መብት ከጣሰ በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ውል መሠረት.ውሉን በፈረሙበት

ሃሮች ይህ ሀገር ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሁለትዮሽ አሠራር አንድ ሀገርሙሉ በሙሉ ወይም በትክክልበዓለም አቀፍ ውል ላይ ያሉትን ህጎች(ደንቦች) ካላከተተ (ካላሸጋገረ) መብቱ የተጣሰበት የዛ ሀገር ዜጋ መንግሥትን በሀገሩ ፍ/ቤት

ለመክሰስ ችግር ይገጥመዋል፡፡ ለዚህ መፍትሔዎች ይኖራሉ፡፡ ይህም ጉዳዩን ወደ አለም አቀፍ ተቆጣጣሪ አካላት ወይም ወደ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤቶች ማቅረብ ነው፡፡

ሌላ በሁለቱ ሥርዓቶች መካከል ሊመደብ የሚችል ሦስተኛ አሠራር አለ፡፡ በዚህ አሠራር ዓለም አቀፍ ሕግ በተለየ ሁኔታ የሚታይሲሆን በአንዳንድ ሁኔታዎች ምንም የማሸጋገሪያ ሕግ ማውጣት ሳያስፈልግ በሃገራቱ ውስጥ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ ይህ አሠራር በብዙ ሃሮች ተቀባይት ያገኘ ነው፡፡ የዓለም አቀፍ ሕግ ከእነዚህ አሠራሮች አንዱን እንዲከተል አንድን ሃገር አያስገድድም፡፡ ሁሉም ሥርዓቶች መልካም ናቸው፡፡ ነገር ግን የእያንዳንዳቸውን ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

የሁለቱ እዩሽ ሥርዓት ትልቁ ድክመት ዓለም አቀፍ ሕግ ይህንንሥርዓት የሚከተሉ ሀገሮች ውስጥ የሚሠራው ስምምነቱን ስላላጸቁ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ በሚወስዱት እርምጃ ለይ ተመሥርቶ መሆኑ ነው፡፡ መንግስታቱ ሲጀመር ዓለም አቀፍ ሕጉን ወደ ብሔራዊ ሕግ ማሸጋገር ያለባቸው መሆን አለመሆኑን ካሸጋገሩም መቼ እንደሚሆን ብቻ ሳይሆን በምን ያህል መጠን እንደሚሠራ ይወስናሉ፡፡

በሌላ አባባል የሁለት እዮሽን ሥርዓት በሚከተሉ ሀገሮች ውስጥ ዓለማቀፍ ሕግከነአካቴው ሰይሸጋገር ሊቀር የሚችልበት ያለበዚያም በአዝጋሚ ሁኔታ እና በከፊል ብቻ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ በተለይ ዓለምአቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕጎች የመንግሥትን ሥልጣን የሚገድቡ በመሆናቸው የዚህ አሠራር ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ሀገሮች አሀዳዊ ወይም መካከለኛ አሠራር እንዲከተሉ መወትወታቸው ብዙም አይደንቅም፡፡

በሌላ በኩል የአሀዳዊ እና የመካከለኛ ሥርዓት ትልቁ ድክመት ፍ/ቤቶች ላይ ትልቅ ጫና የሚያሳድሩ

መሆናቸው ነው፡፡ ዳኞች ዓለምአቀፍ ሕግን ሥራ ላይ ለማዋል ስለሕጉ መረጃ ሊኖራቸው እና ስለአተረጓጎሙ ሥልጠና ሊወስዱ ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ሌላው አስሳቢ ችግር በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ዳኞች ዓለም አቀፍ ሕግን በተለያየ መንገድ መተርጎማቸው እና መተግበራቸው ነው፡፡

**በዚህ ክፍል የተነሣው ሃሣብ ሁሉ አቀፍ ስለመሆኑ**

በዚህ ክፍል ውስጥ የሀገር ውስጥ የሕግ የበላይነት ለምን በዓለምአቀፍ ሕግ የበላይነት ላይ ጥገኛ እንደሚሆን ለማስረዳት የሰብዓዊ መብት በምሣሌነት ቢወሰድም ለሌሎች ብዙ ዓይነት ሕጎችም አግባብነት እንዳለው መታወቅ አለበት፡፡ አዕምሯዊ ንብረትን ለመጠበቅ የተደረጉትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም በዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት ሥር የተደረጉትን የንግድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ልዩ ልዩ ስምምነቶችን በምሣሌነት መጥቀስ ይቻለል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት የሙግት መፍቻ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ሕግን የማስፈፀም ብቃት ያለው መሆኑን መጥቀስ ይገባል፡፡

## 4.3 በዓለምአቀፍ ደረጃ ያለው የሕግ የበላይነት በብሔራዊ ሕግ ላይ ለምን ጥገኛ እንደሚሆን

ነገሩን አዙረን ስንመለከተው በአገር ውስጥ ደረጃ የሚኖረው የሕግ የበላይነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚኖረው የሕግ የበላይነት ብዙ ጠቀሜታዎች ይሰጣል፡፡ በእርግጥም የዓለምአቀፍ የሕግ የበላይነት በአገሮች ውስጥ ሕግ በሚተገበርበት ሁኔታ ላይ በጣም ጥገኛ ነው፡፡

**የሕግ አውጪዎችና የመስተዳድሮች ድርሻ**

እዚህ ላይ የሕግ አውጪውና የሕግ አስፈጻሚው (መስተዳድር) ድርሻ ችላ ሊባል አይችልም፡፡ በተለይም በመንግሥት መስተዳድር ተፈርሞ በፓርላማ የጸደቀ ሕግ በሀገር ውስጥ በቅጡ መተግበር ያለበት መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ከላይ በተ.ቁ. 4.1 እና 4.2 የተብራራውን ይመለከታል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፉናበብሔራዊ የሕግ የበላይነት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አንድ ከበድያለ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ ከላይ በተ.ቁ 3.2.3 ሥር የየተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ም/ቤት አባላት(ቋሚ አባላትን ጨምሮ) የየተባሩትን መንግሥታት ቻርተር (መተዳደሪያ ደንብ) እንደሚጥሱ ተነስቷል፡፡

ይህን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ2003 (በ1995 ዓ.ም) ከኢራቅ ጋር የተደረገው ውጊያ ባሳዛኝነቱ ይጠቀሳል፡፡

በዚህ ጦርነት ውስጥ መንግሥታት ዓለምአቀፍ ሕግንም ሆነ ብሔራዊ ሕጋቸውን በመጣስ ተካፍለዋል፡፡ የመንግሥታቱ መሪዎች ብሔራዊ ጥቅማችን ያስገድደናል በሚል ሕገወጥ ጦርነቱ ውስጥ ለመግባት ወስነዋል፡፡የሕግ የባላይነት መርሕን ለመጣስ ዝግጁነታቸውን አሳይተዋል፡፡ እንዲሁም ሀገሮች የሚወስዷቸው የፀረሽብር እርምጃዎች ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት መስፈርቶችን የሚፃረሩ መሆናቸውም በምሳሌነት ሊነሣ የሚችል ነው፡፡

ይህ የወደፊቱን የዓለማችንን ሰላምና ፀጥታ አደጋ ላይ የሚጥል ከባድ ነገር በመሆኑ በጥልቀት መታየት ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ በዚች አነስተኛ መመሪያ ውስጥ ይህንን መዳሰስ ባይቻልም ቢያንስ ሳይጠቀስ ማለፍ አግባብ አይሆንም ፡፡

የሕግ የበላይነት ለሁሉም ሰዎች ሁሉጊዜ የሚሠራ መሆን አለበት፡፡ መግባባት ካለ የሕግ የበላይነትን ሥራ ላይ ማዋል ቀላል ነው፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው ከፍተኛ የሆነ የአስተሳሰብ አለመጣጣም ካለ የሕግ የበላይነት መሥራት አይቻልም የሚል አመለካከት ያላቸው አሉ፡፡

የታላላቆቹ በተለይም የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት አባል መንግሥታት ባህርይ ለዓለም ሰላም እና ደህንነት ወሣኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በተለይ የምዕራባዊያን መንግስታት በዚህ በኩል ግንባር ቀደሙን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ቢያንስ በዚህ በኩል የሚስነቅፍ ባህርይ ሊኖራቸው አይገባም፡፡ በገሃድ የሚታየው ግን ከዚህ የተለየ መሆኑ ያሳዝናል፡፡

## የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ሚና

ዓለም አቀፍ ሕግን በብሔራዊ ደረጃ እንዲተገበር በማድረግ ፍ/ቤቶች በጣም ወሣኝ ሚና እንደሚጫወቱ ግልፅ ነው፡፡ ፍ/ቤቶች መንግስትም ሆነ ድርጅቶችና ግለሰቦች በዓለምአቀፍ ሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲወጡ ያደርጋሉ፡፡ ለወደፊት የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች የህግየበላይነት በዓለምአቀፍ ደረጃም ጭምር እንዲሰፍን ለማድግ ከፍ ያለ ሚና እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው፡፡

ከዚህ ላይ ግን የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ያላቸው ሚና የተገደበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለምሣሌ በሌላ አገር ውስጥ በውጪ ዜጋ የተፈፀመ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ለማየት ቢችሉም የአለምአቀፍ ሕግ በሚመለከታቸው መንግሥታት፣ሌሎች አካላት ወይም ግለሰቦች መካከል የሚነሳውን ማናቸውንም ዓይነት የዓለምአቀፍ ሕግ ክርክሮችን መዳኘት ግን አይችሉም፡፡

ነገር ግን የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ዓለም አቀፍ ሕግን በማስፈፀም ሚና በሚኖራቸው ጊዜም ባብዛኛው ዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ይግባኝ እንዲሰሙ ደረጋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክያት አንድም ዓለም አቀፍ ሕግ አንድ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተገበርና በሌላ በኩል የውሳኔዎቹንም ጥራት ለመቆጣጠር ሲባል ነው፡፡

ለምሳሌ የአውሮፓ ሀገራት ብሔራዊ ፍ/ቤቶች የአውሮፓ የሰብዓዊ መብት ስምምነትን ስራዬ ብለው ማስፈፀም ቢጀምሩ የአውሮፓው የሰብአዊ መብት ፍ/ቤት የሰብዓዊ መብት ስምምነቱን በመተረጎም እና በመተግበር ረገድ የመጨረሻው ዳኝነት ሰጪ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው፡፡

ይህ ማለት ግን ከላይ እንደተብራራው የብሔራዊ ፍ/ቤቶች መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላትና ግለሰቦች በዓለም አቀፍ ሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲፈፅሙ በማድረግ ለወደፊቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕግ በላይነት እንዲሰፍን ለማድረግ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ሳይዘነጋ ነው፡፡

## የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ

መጀመሪያ ነገር የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች የአለም አቀፍ ፍ/ቤቶችን ወይም የዳኝነት ሰጪ አካላትን የሥልጣን ክፍተት ሊያሟሉ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛ ብሔራዊ ፍ/ቤቶች እራሳቸውን አቅምን ያገናዘበና ፈጣን አማራጭ አድርገው ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ይህ የሕግ የበላይነት ፍትሕ ለሁሉም ተደራሽ እና የተፋጠነ እንዲሆን ካለው ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡

ሶስተኛ መንግስታት በብዛኛው በዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ሲጀመር ዓለም አቀፍ ሕግ የመንግሥታትን ስልጣን ይገድባል፡፡ የበለጠ ደግሞ ዓለምአቀፍ ፍ/ቤቶችየስልጣናቸውን ልክ እንዲያስቀምጡላቸው መንግሥታትአይፈልጉም፡፡ ይልቁንም የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች የተሻለ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን ይህ ደግሞ ፍርዳቸውን ተፈፃሚ እንዲሆን ስለሚያግዝ ለሕግ የበይላይነት መስፈን ይረዳል፡፡

በአራተኛ ደረጃ የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ዓለም አቀፍ ሕግን ከሀገር ውስጥ ተጨባጭ እውነታ ጋር ለማገናዘብ የተሸለ እድል አላቸው፡፡ ስለብሔራዊ ሕጎችና አተገባበራቸው የተሻለ እውቀትና ልምድ አላቸው፡፡ በተለይ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ለብሔራዊ ህጎችና እሴቶች ከግምት ውስጥ እንዲገቡ የተወሰነ ቦታ የሚተው እንደመሆናቸው የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ይህንን የተሻለ ሊያገናዝቡ ስለሚችሉ በሀገር ውስጥ መዳኘቱ የራሱ ጠቀሜታ አለው፡፡ የአገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ፍርድ በዚህ ረገድ በመንግስታትም ሆነ በህዝቡ የተሸለ ተቀባይነት የማግኘትና የመከበር ዕድል አለው፡፡

አምስተኛ  የሀገር ውስጥ ፍ/ቤቶች ዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶችን ከብዙ ስራና በጉዳይ ከመጥለቅለቅ ሊታደጓቸው ይችላሉ፡፡ በአህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ላይ ወደ አህጉራዊ ፍ/ቤት ጉዳዩ ከመምጣቱ በፊት አገራዊ መፍትሄዎችን አሟጦ መጨረስ ያበት መሆኑ የሚቀመጠውምለዚሁ ነው፡፡

***የመተጋገዝ መርህ***

በሮሙ ዓለም አቀፍ ወንጀል ፍ/ቤት መተዳደሪያ ደንብ ላይም ይሄው የመተጋገዝ መርህ ተቀምጧል፡፡ ሀገሮችን ጉዳዮችን ለመዳኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ካሟሉ ዓለም ዓቀፍ ወንጀሎችን ለማየት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው፡፡

የሕግ የበላይነት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚሰፍነው በዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶችና ፍርድ ሰጪ አካላት ብቻ ከሆነ እነዚህ የፍትህ አካላት ወደ እነሱ የሚጎርፈውን ብዛት ያለው ጉዳይ ማስተናገድ ስለሚሳናቸው የፍትህ መዘግየት ብሎም መታጣት ሁኔታን ያስከትላል፡፡

ብሔራዊ ፍ/ቤቶች የተጠቀሰውን ሚና ከተጫወቱ ጥራታቸውን የጠበቁ መሆን እንዳለባቸው ግልፅ ነው፡፡ በተለይ ነፃነትንና ገለልተኝነትን ጨምሮ በብሔራዊ ደረጃ ለህግ የበላይነት መስፈን መሟላት ያላባቸው መስፈርቶች መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

ነገር ግን ፍ/ቤቶች በዜጎች በሙስና እንደተዘፈቁ ሆነው የሚቆጠሩ ከሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነትን ለማስፈን ገንቢ አስተዋፆኦ አይኖረውም፡፡ በሌላ አነጋገር የየሀገራትን ፍ/ቤቶች ጥራት ማሻሻል ለብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ለዓለምአቀፍ የህግ የበላይነት የራሱ የሆነ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

## 5. ተጨማሪ ምንባብ ምንጮች

ለተጨማሪ ንባብ በራውል ዋለንበርግ የሰብዓዊ መብትና የጦር ሰብዓዊነት ኢኒስቲትዩትእና በሄይግ የህግ ዓለም ዓቀፋዊነት ኢኒስቱቲዩትድረ ገፅ ላይየሚከተሉት ድርገፆች በዋቢነት ተጠቅሰዋል፡-

የራውል ዋለንበርግ የሰብዓዊ መብትና የጦር ሰብዓዊነት ኢኒስቲትዩት

http://www.rwi.lu.se/

የሄይግ የህግ ዓለም አቀፋዊነት ኢኒስቲትዩት

http://www.hiil.org/

የፓርላማዎች ዓለም ዓቀፍ ሕብረት ድረገጽ

http://www.ipu.org/english/home.htm

የዓለም የፍትህ ፕሮጀክት ድረገጽ

http://worldjusticeproject.org/

የሚከተሉት ሕትመቶች በተለይ በምንጭነት ተጠቅሰዋል:-

የቀድሞ ርዕሳነ ብሔርና መንግሥታት የጋራ መርሐግብር 26ኛ ዓመታዊ የምክክር ሥብሰባ ማጠቃለያ

http://www.interactioncouncil.org/final-communiqu-29

ሰብዓዊ መብት፣ ለፓርላማ አባላት የተዘጋጀ ማስታወሻ፣ በፓርላማዎች የጋራ ሕብረት እና በተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር በጋራ የታተመ እ.ኤ.አ 2005

http://www.ipu.org/PDF/publications/hr_guide_en.pdf

ፓርላማ እና ዲሞክራሲ በ21ኛው ክ/ዘመን፤ የትግበራ መመሪያ፣ በፓርላማዎች የጋራ ሕብረት የታተመ፣ እ.ኤ.አ 2006

http://www.ipu.org/PDF/publications/democracy_en.pdf

ደህንነት በፓርላማ እይታ፤ በፓርላማ የጋራ ሕብረት እና በጄኔቫ የጦር መሣሪያ ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር ማዕከል በጋራ የታተመ

http://www.ipu.org/PDF/publications/decaf-e.pdf

ሰብዓዊመብትናፓርላማዎች፣ለአባላትናለሠራተኞችማስታወሻ፣የዌስትሚኒስትርቡድን፣ ዓለምአቀፍየጠበቆችማህበርናዩኬኤይድእ.ኤ.አ. 2011

http://www.ibanet.org/Human_Rights_Institute/About_the_HRI/HRI_Activities/Parliamentary_Strengthening.aspx

የብሔራዊ ተቋማትን የሚመለከቱ መርሖዎች (የፓሪስ መርሖዎች)

http://www2.ohchr.org/english/law/parisprinciples.htm

በዓለም የፍትሕ ፕሮጄክት ሥር የተዘጋጀ የሕግ የበላይነት ኢንዴክስ

http://www.worldjusticeproject.org/rule-of-law-index/